


# አማርኛ



## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህሩ መምሪያ



፬ኛ ክፍል

# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፪(2)ኛ ክፍል


**አስማምቶ አዘጋጆች፡-**

**መሣይ ለማ መንሾ (MA)**

**አማኑኤል ዮናስ አበበ (MA)**

**ፀሐይ ደረሰ ካሴ (MA**

## ማውጫ


**ይዘት** **ገጽ**

ምዕራፍ አንድ ....................................................................................1

ልብስ ...............................................................................................

ምዕራፍ ሁለት ..................................................................................18

**ወቅቶች**

ምዕራፍ ሶስት ...................................................................................29

ታሪኮች ...........................................................................................

ምዕራፍ አራት...................................................................................41

የአትክልት ቦታ ................................................................................

ምዕራፍ አምስት.................................................................................57

የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ...................................................................

ምዕራፍ ስድስት .................................................................................70

ባህላዊ ሙዚቃ ..................................................................................

ምዕራፍ ሰባት...................................................................................80

መልካም ስነ ምግባር ..........................................................................

ምዕራፍ ስምንት.................................................................................83

የምግብ አዘገጃጀት .............................................................................

ምዕራፍ ዘጠኝ ...................................................................................109

ዲጅታል ቁስ.............................................................................................
ምዕራፍ አስር...........................................................................................119
የዱር እንስሳት ........................................................................................

## መግቢያ

### ለተጠቃሚዎች

ይህ መጽሐፍ የ፪ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ለመጀመሪያ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የሚማሩ ተማሪዎች በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ ስርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡

መጽሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ በእኩል ደረጃ እንዴት እንደሚማሩ ማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች አካቷል፡፡

### መርህ አንድ

ተማሪዎች ስዕሎችንና ርዕሶችን በመመልከት የቅድመ ማዳመጥና ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲገምቱ በማድረግ ተረቶችን ወይም ታሪኮችን በማዳመጥና በማንበብ የማዳመጥና የማንበብ፣ የመጻፍና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፡፡

## መርህ ሁለት

ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ታሪክ ወይንም ንባብ በሚገባ በማዳመጥና በማንበብ የአዳምጦ/የአንብቦ መረዳት በንግግርም ሆነ በፅሁፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ በተከታታይ የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ

## መርህ ሶስት

ልምምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡

ተማሪዎች ባዳመጡትና ባነበቡት ፅሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን እንደየአጠያየቃቸው የሚወክሏቸውን ፍቺ በመፃፍ በተገቢው የቃላት አሰዳደር ስርዓት በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያለማምዷቸው፡፡

## መርህ አራት

ተማሪዎች በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሰረቱ ዓረፍተነገሮችን ማንበብ እንዲችሉ ልልምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡

## መርህ አምስት

ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቻቸውን አብረው መማር አለባቸው፡፡ በዚህም የሚያደምጡትንና የሚያነቡትን ሃሳብ ይረዳሉ፡፡ የቃላት እውቀታቸውንም በማሳደግ በንግግርና በፅሁፍ ሃሳባቸውን በአግባቡ ይገልፃሉ፡፡

# ለመምህራን

ውድ መምህር ተማሪዎች የቋንቋን ትምህርት በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባትተማሪዎችን በሚገባ ሊያግዟቸው ይገባል ፡፡

፩. ለተማሪዎች የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን… ይንገሯቸው/ ያንብቡላቸው፡፡/

፪. ለተማሪዎች የነገሯቸውን/ ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ተማሪዎች መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ እንዲሁም የራሳቸውን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

፫. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችንና ተግባራትን እንደየመመሪያቸው በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው፡፡

፬. ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

፭. ለተማሪዎች በቤታቸው ተዘጋጅተው በመምጣት በተግባር እንዲያሳዩ የተለያዩ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

አማርኛ

፩ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አንድ

# ልብስ

18

ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

- ካዳመጡት ጽሑፍ አጠቃላይ ሐሳብ ይለያሉ
- ከተሰጣቸው ፅሑፍ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ ይለያሉ
- ለተለመዱ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ
- ባለ ሶስት ሆሄ ቃላትን ያጣምራሉ ይነጥላሉ
- ሆሄያትን አቀናጅተው ቃላት ይፅፋሉ

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማንበብ
- የፅህፈት ትክክለኝነት
- ድምፀት

## ((( ማዳመጥ

# ልብስና መስሪያዎቹ

## መምህር፡-

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- የሚከተለውን ምንባብ እንደተማሪዎች ሁኔታ በተመጠነ ድምጽና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በምንባቡ መካከል ያለውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ ከምንባቡ መካከል ላይ ሲደርሱ ተማሪዎችን በመጠየቅ ስለወደፊቱ ሀሳብ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡

ልብስ ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ልብስ ማለት ለሰውነታችን ከለላ በመሆን ሠውነታችንን ከብርድ፣ ከፀሐይና ከመሳሰሉት የሚከላከልልን ነው፡፡

*…ተማሪዎች ልብስ ከምን ከምን የሚሰራ ይመስላችኋል?…*

ልብስ ከተለያዩ የመስሪያ ቁሶች ይዘጋጃል፡፡ ይኸውም ከጥጥ፣ ከቆዳ (ሌጦ)፣ ከሱፍ ወዘተ. ይሰራል፡፡ ከጥጥ ጋቢ፣ ሂጃብ፣ነጠላና የሐበሻ ቀሚስ ሲሰራ ከቆዳ ኮት፣ ጃኬት፣ ኮፍያ፣ ሱሪ፣ ወዘተ. ከሱፍ ደግሞ ሱሪ፣ ኮት፣ ጃኬት፣ … ይሰራሉ፡፡

**መምህር፡-**

- ❖ በተማሪ መጽሐፉ ያሉትን የአዳምጦ መናገር ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሰጡት ምላሽ በቂ ግብረ መልስና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

## 🗝 ቃላት

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያሉትን የተጓደሉ ፊደላትን በጽሑፍ እንዲያሟሉ ያግዟቸው፡፡
- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በትዕዛዝ ፪ ላይ ያሉትን ቃላት ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላት እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባሩ መልስ (ትዕዛዝ ፪)**

1. በቀለ
2. ነጠቀ
3. ለማዳ
4. ደለበ
5. ብስል

## ☞ ሞክሼ ፊደላት

**መምህር፡-**

- ስለሞክሼ ፊደላት ምንነትና አይነት በቂ ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡ ፡
- ተማሪዎች የሞክሼ ፊደላቱን ቅርጽ፣ ስያሜና ዝርያ በደብተራቸው ፅፈው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ሞክሼ ፊደላትና ዝርያቸው የያዙትን ቃላት ከዓረፍተ ነገሮች ውስጥ እንዲለዩና ሞክሼ ፊደላትን በመነጠል እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ የመማር ማስተማሪያ ዘዴዎትን እገዛ ከሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ሁኔታ ጋር አስማምተው ያቅርቡ፡፡

| ሀሌታው (ሀ) | ሐመሩ (ሐ) | ብዙኀኑ (ኀ) |
|---|---|---|

| | |
|---|---|
| ንጉሡ (ሠ) | እሳቱ (ሰ) |
| አልፋው (አ) | ዐይኑ (ዐ) |
| ጸሎቱ (ጸ) | ጻዲቁ (ፀ) |

## 🕮 ንባብ

# የበዓል ልብስ

**መምህር፡-**

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን “የበዓል ልብስ” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- ➢ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ላይ “የበዓል ልብስ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያግዟቸው፡፡
- ➢ በመቀጠል የንባብ መከታተያ ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ተማሪዎች ሲያነቡ ደቂቃ በመያዝ የንባብበቡ ችሎታቸውን እየገመገሙ ማበረታቻና አስተያየት ይስጧቸው፡፡
- ➢ በተጨማሪም ተማሪዎች ሌሎች አጫጭር ፅሁፎችን ሰዓት(ደቂቃ) ተይዞላቸው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡
- ➢ በተግባሩም የንባብ ፍላጎታቸው መሻሻሉን ይከታተሉ፡፡
- ➢ የንባብ ፍጥነታቸውን ለመከታተልም የወሰደባቸውን ጊዜ በሰንጠረዥ ላይ በመመዝገብ ይከታተሉ፡፡

## 🗝 ቃላት

**መምህር፡-**

- ስለተመሳሳይ የቃላት ፍቺ ማብራሪያና ምሳሌ ከሰጡ በኋላ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ትዕዛዝ ፩ን የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባሩ መልስ (ገጽ 7 ትዕዛዝ ፩)**

1. ሠ
2. ሐ
3. ለ
4. ሀ
5. መ

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፪ ላይ በስዕል የቀረቡትን አልባሳትና ቀለሞችን በሚገባ እንዲገነዘቧቸው ምሳሌውን ያብራሩላቸው፡፡
- ከዚያም ወደቃል በመቀየር እንዲፅፉና እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ሆሄ የተቀረፀባቸው ስዕሎች፣ ፍላሽ ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆች፣ ካርቱኖች፣ ጥቁር ሰሌዳ … ይጠቀሙ፡፡

☞ውስብስብ ፊደላት

**መምህር፡-**

- ስለውስብስብ ፊደላት ምንነት ገለፃ ከሰጡ በኋላ በተማሪ መጽሐፍ ላይ በቅደም ተከተል የተቀመጡትን ውስብስብ ፊደላት ተማሪዎቹ ተራ በተራ እየተነሱ እንዲነቧቸው ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪቹን በቡድን በማስቀመጥ በምሳሌው መሰረት ከውስብስብ ፊደላት መካከል አምስቱን በመምረጥ ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- ተማሪቹ በቡድን በመሆን በውስብስብ ፊደላት የመሰረቱትን ቃላት በሚገባ ተመልክተው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

☞ ማጣመርና መነጠል

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ገጽ 10 ትዕዛዝ ፩ ላይ የቀረቡትን ውስብስብ ፊደላት ነጣጥለው እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠል ተማሪ መጽሐፍ ገጽ 10 ትዕዛዝ ፪ ላይ የቀረቡትን ፊደላት በማጣመር ውስብስብ ፊደላት እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ነጣጥለውና አጣምረው ለፃፉቸው ውስብስብ ፊደላት እርማት ይስጧቸው፡፡

✍ መፃፍ

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት የተለያዩ ድርጊታዊ ገለጻዎችን ለተማሪዎቹ በሚገባ በማሳየት ድርጊቱን በቃላት እንዲፅፉ አድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎቹ ድርጊታዊ ገለጻውን በሚገባ በቃላት መግለፃቸውን ያረጋግጡ፡፡ ከዚያም ተማሪዎችም እርስ በርስ ድርጊታዊ ገለጻዎችን እየተገበሩ በቃላት እየተከሉ ተግባሩን የበለጠ እንዲያዳብሩት ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- የሚከተሉትን ቃላት ድምፅዎን ከፍ አድርገው በመናገር ተማሪዎቹ እንዲፅፏቸው ያድርጉ፡፡

1. አሯሯጠ
2. አሟላ
3. ፏፏቴ
4. ትምህርቷ
5. እጇ

## ☞ስርዓተ-ነጥብ

**መምህር፡-**

- ✓ ስለስርዓተ-ነጥብ ምንነትና ጠቀሜታ በግልፅ ውይይት ያድርጉ፤
- ✓ ተማሪዎችን በጥንድ ያስቀምጧቸውና የሚከተለውን ፅሁፍ በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡

መምህሩ ወደክፍል ገቡ፡፡ "ተማሪዎች እንደምን አደራችሁ?" በማለት ሰላምታ ሰጡ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹን እየዞሩ መመልከት ጀመሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ትኩረታቸውን ወደመምህሩ አደረጉ፡፡ የመምህሩ አተያይ ተማሪዎችን አስደነቃቸው፡፡ መምህሩም "አስቴር ለምን የደንብ ልብስሽን አለበስሽም?" በማለት ጠየቋት፡፡

- ✓ በሰሌዳ ላይ የፃፉትን ጽሁፍ (አራት ነጥብና የጥያቄ ምልክትን ብቻ) ከጽሁፉ ውስጥ በማስወገድ ተማሪዎች ጽሁፍ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ አራት ነጥብና ጥያቄ ምልክት የሌለበትን ጽሑፍ ሲያነቡ በንበታችሁ ላይ ምን ምን ለውጥ እንዳዩ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም አንድ ፅሁፍ ከነስርዓተ-ነጥብና ከስርዓተ-ነጥቡ ውጪ ሲነበብ ያለውን ልዩነት ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ ስርዓተ-ነጥቦች በንበት ሥርዓታችን ላይ ያላቸውን ሚና በማስመልከት በቂ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፪ ያለውን ተግባር ከማሰራትዎ በፊት የህይወት ታሪክ ማለት ስለራስ ማንነት የሚገልፅ፤ ራስን የማስተዋወቂያ መንገድ፤ እንደሆነ ለተማሪዎቹ ምሳሌ እየጠቀሱ አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም አራት ነጥብን በመጠቀም የህይወት ታሪካቸውን የሚገልፁ አምስት በዓረፍተነገሮች እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ልብስና መስሪያዎቹ የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ ሞክሼና ውስብስብ ቃላትን እንዲለዩና በእነሱም ቃላትን እንዲመሰርቱ፤ የፊደላትን ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላትን እንዲያዋቅሩ ተደርጓል፡፡ "የበዓል ልብስ" የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ፤ በተጨማሪም ስለሥርዓተ ነጥብ ምንነትና አጠቃቀም እንዲረዱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

| አማርኛ ፪ኛ ክፍል | ምዕራፍ ሁለት ወቅቶች | 18 ክፍለ ጊዜ |
|---|---|---|

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ፅሁፍን በማዳመጥ የተለየውን ሐሳብ ይፅፋሉ
- የምንባቡን ይዘት በቃላቸው ይናገራሉ
- ከ"ወቅቶች" ጋር ለተገናኙ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ
- ድምፆችን ያጣምራሉ፤ይነጥላሉ
- ባለ አራት ፊደል ተዘውታሪ ቃላትን ይፅፋሉ
- አራት ነጥብን ይለያሉ

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማንበብ
- ፅህፈት
- ድምፀት

## ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- ✓ የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡
- ✓ በሚያስተምሩበት ጊዜ በመማሪያ ክፍሉ አካባቢ ያለውን ሁኔታ ተመልክተው ምን ዓይነት ወቅት እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ ስዕሎችን እንዲገምቱ የመነሻ ሐሳብ ይሰጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሚገምቷቸውን አንዳንድ ሐሳቦች ለናሙና ያህል በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ እንደሁኔታው የአካቶ ትምህርትን ይተግብሩ፡፡
- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱን ከ3-5 ደቂቃ ባለ ጊዜ ውስጥ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡

## ኢትዮጵያና ወቅቶቿ

በኢትዮጵያ አራት ወቅቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- ክረምት፣መኸር (መፀው)፣ በጋ (ሐጋይ) እና በልግ (ፀደይ) ናቸው፡፡ ክረምት የሚይዘው ሰኔ፣ ሐምሌ፣ ነሐሴና ጷጉሜ ወሮችን ነው፡፡ መኸር (መፀው) መስከረም፣ ጥቅምትና ህዳር ወሮችን ያካትታል፡፡

**ተማሪዎች በጋ እና በልግ ወቅቶች ምን ምን ወራትን የሚይዙ ይመስላችኋል?**

በጋ ታህሳስ፣ ጥር እና የካቲትን የሚይዝ ሲሆን በልግ ደግሞ መጋቢትን፣ ሚያዚያንና ግንቦትን ያጠቃልላል፡፡

## አዳምጦ መናገር

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች የምንባቡን አንኳር ነጥብ ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን መሰረት አድርገው በመማሪያ መፅሃፉ ላይ የቀረቡትን የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች ያሰሩዋቸው፡፡እርማትም ይስጧቸው፡፡

የተግባሩ መልስ

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት

## 🗝 ቃላት

**መምህር፡-**

- ✓ የማዛመድ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ተግባር (ወቅቶችን ከወራት ጋር ማዛመድ) እንዲያዛምዱ ያድርጉ፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሽ ይቀበሏቸው፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡
- ✓ የቃላት ሲያሰሩ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችንም ታሳቢ ያድርጉ፡፡

**የተግባሩ መልስ**

| | |
|---|---|
| 1. ለ | 3. መ |
| 2. ሀ | 4. ሐ |

- ✓ ተማሪዎች ቻርቱ ውስጥ ባለ አራት ድምፅ ወራትን እንዲፅፉ ያድርጓቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ጥቅምት | መጋቢት |
| ታህሳስ | ሚያዚያ |
| የካቲት | ግንቦት |

- ✓ በመማሪያ መፅሃፉ በቻርት መልኩ የቀረበውን የሳምንቱ ቀናትን ተግባር ያሰሯቸው፤ ምላሽ ይስጧቸው፡፡

## 🕮 ንባብ

**መምህር፡-**

- ✓ ከምንባቡ በፊት የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ከ3-5 ባለው ደቂቃ ውስጥ ያሰሯቸው፤ተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልሶችና ግምቶች የተወሰኑትን በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የ"አበባ አየሁሽ" ጭፈራውን ሌሎች ተማሪዎችን በማይረብሽ መልኩ ከክፍል ውጪ እንዲተገብሩት ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ አተገባበሩም፡- አንዲት መሪ (አውጪ) እና ሶስት ተቀባይ ተማሪዎች ሆነው በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት ለፊት እንዲወጡ ያድርጉ፤ በመቀጠል ጭፈራውን እየተቀባበሉ እንዲተገብሩት ያድርጉ፡፡
- ✓ እንደ ትምህርት ቤቱና መማሪያ ክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጭፈራውን እንዲተገብሩት ማድረግም ይችላሉ፡፡
- ✓ ከላይ ከተቀመጠው አተገባበር ባሻገር እርስዎ የራስዎን የማስተማር ስነ-ዘዴ መተግበር ይችላሉ፡፡
- ✓ በመቀጠል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ባማከለ መልኩ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን ሌሎች የበዓላት መዝሙሮች፣ ጭፈራዎች፣ ጨዋታዎች ወዘተ. እቤታቸው ተለማምደው መጥተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ በቤት ስራ መልኩ ይስጧቸው፡፡

## ☞ መነጠልና ማጣመር

**መምህር፡-**

- ✓ መነጠልና ማጣመርን በተመለከት ምንነቱንና ጠቀሜታውን ለተማሪዎች ያስረዷቸው፡፡

**መነጠልና ማጣመር**

ይህ ድምፆችንና ቃላትን በማንበብና ወደ ተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ልጆቹ ድምፆችንና ቃላትን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ስርዓት እንዲፅፉ ያደርጋቸዋል፡፡

**ማጣመር፡-** ሲባል ድምጾቹ/ቃላቱ የተመሰረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሃዶች ለየብቻ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይጠሯቸዋል፡፡

**መነጠል፡-** ደግሞ ቃላቱን ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላት ወይም ወደ አነስተኛ አሐዶች ይነጥላሉ፡፡

- ✓ ከላይ ያለውን ፅንሰ ሃሳብ በቃል ካስረዷቸው በኋላ ምሳሌ ይስጧቸው፤ በመቀጠል ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተጨማሪ የክፍል ስራ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ቃላትን ከአብዥ ቅጥያ “ዎች” ጋር በማጣመር ተማሪዎቹ ተግባሩን እንዲሰሩ አጭር ገለጻና ምስሌ በመስጠት እንዲሰሩ ያግዟቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

- ✓ በመቀጠል በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ፊደላት በማገጣጠም ቃላትን የመመስረት ተግባርን በጥንድ በመሆን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

**መልስ፡- -ቀጠረ -ረጠበ -በረት -ተመለከተ…**

- ✓ ቃላት በሚለው ርዕስ ስር ያለውን ተግባር በምሳሌው መሰረት ያሰሯቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- ✓ "**አካባቢያችንን እንጠብቅ**" በሚል ርዕስ ስር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እየደጋገሙ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ✓ አልፎ አልፎ አንዳንድ ተማሪዎች ቆመው ድምፅ በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻቸው ደቂቃ እየመዘገቡ እንዲያነቡ ድርጓቸው፡፡(ደቂቃውን መምህሩ ቢይዝስ)
- ✓ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ያማከለ አቀላጥፎ የማንበብ ተግባር ያከናውኑ፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡

## ✍ መፃፍ

**መምህር፡-**

- ✓ የሚከተሉትን ቃላት እያነበቡላቸው በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በወረቀት ፅፈው ይስጧቸው፡፡
- ✓ ቃላት
    - ተዘጋ
    - ተማረ
    - አወጣ
    - ጠላት
    - ኩራት
- ✓ ተማሪዎች ከላይ ያሉትን ቃላት ካፃፉቸው በኋላ የመጀመሪያ ፊደላቸውን እያጠፉ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ በመቀጠል ባጠፉቸው ፊደላት ምትክ ሌላ ፊደል ተክተው ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

**መልስ**

1. ተዘጋ = ዘጋ = አዘጋ (ሌላም ፊደል ሊተኩ ይችላሉ።)
2. ተማረ = ማረ =አማረ (ሌላም ፊደል ሊተኩ ይችላሉ።)
3. አወጣ = ወጣ =ተወጣ (ኃላፊነቱን ተወጣ)
4. ጠላት = ላት = አላት (ሌላም ፊደል ሊተኩ ይችላሉ።)
5. ኩራት = ራት =አራት (ሌላም ፊደል ሊተኩ ይችላሉ።)

- ✓ ተማሪዎች በቡድን በመሆን መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን ቃላት በተለያዩ ዓ.ነገሮች ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ፍቺ እንዲኖራቸው ያድርጉ።
- ✓ በየቡድኑ እየተዘዋወሩ ያግዟቸው፤ይምሯቸው።

**የተግባሩ መልስ**

1. ሄደ፡- ሰዓቱ **ሄደ**።

   ልጁ ወደ ትምህርት ቤት **ሔደ**።

2. ዓይኖች፡- የባትሪው **ዓይኖች** ተቃጠሉ።

   የልጁ **ዓይኖች** ትላልቅ ናቸው።

3. ውኃ፡- ከምግብ በኋላ **ውኃ** እጠጣለሁ፡፡

ለበዓል የተዘጋጀው መውደድ **ውኃ** ነው፡፡

4. ጠላ፡- የአስቴር **ጠላ** ይጥማል፡፡

ከማል በቅቤ መብላት **ጠላ**፡፡

5. ተሾመ፡- **ተሾመ** ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

ኢብራሒም የክፍል አለቃ ሆኖ **ተሾመ**፡፡

✓ ለሥርዓተ ነጥብ ማስተማሪያነት የተዘጋጀውን ምንባብ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡ ተማሪዎች ተራ በተራ እየተነሱ በአንቀፁ ውስጥ አራት ነጥብ እንዲያስገቡ ያግዟቸው፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "የኢትዮጵያ ወቅቶች" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ ባለአራት ሆሄ ቃላትን እንዲለዩ፣ የሳምንቱን ቀናት እንዲናገሩና እንዲፅፉ ፤ የፊደላትን ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላትን እንዲያዋቅሩ ተደርጓል፡፡ "አካባቢያችንን እንጠብቅ" የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ በተጨማሪም በአራት ነጥብ ፅሁፍን እንዲያሚሉ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ ከገጽ 15-17 የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

አማርኛ

፱ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሶስት

# ታሪኮች

18

ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ያዳመጡትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ ለይተው ቃላዊ ዘገባ ያቀርባሉ
- ካነበቡት ፅሑፍ ውስጥ አጠቃላይ ሐሳቡን ይፅፋሉ
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ አራት ነጥብን ይጠቀማሉ
- ባለ አራት ፊደል ተዘውታሪ ቃላትን ይፅፋሉ
- ቃላትን እና የጥያቄን ምልክት ይጠቀማሉ

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- ፅህፈት
- ድምፀት

## ማዳመጥ

### ታሪኮች

**መምህር፡-**

- ✓ የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡
- ✓ ስዕሎችን እንዲገምቱ የመነሻ ሐሳብ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነሳሳትና ዝግጁ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ከምንባቡ ጋር ዝምድና ስላለው ተረት ምንነት ይጠይቋቸው፤ አንዳንድ መልሶቻቸውን በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሚገምቷቸውን አንዳንድ ሐሳቦች ለናሙና ያህል በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱን ከ3-7 ደቂቃ ባለ ጊዜ ውስጥ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡

# አውራ ዶሮና ቀበሮ

በጫካ ውስጥ የሚኖር አንድ ቀበሮ አንድ ቀን በጣም ርቦት ከመንደር ውስጥ ገብቶ ሲዞር አውራ ዶሮ በማየቱ በጣም ደስ አለው፡፡ ቀበሮው አውራ ዶሮውን ያየው "ኩኩሉ…" እያለ ሲጮህ ነበር፡፡ ቀበሮውም ወደዶሮው ተጠጋና "ጥሩ ድምጽ ስላለህ እባክህን ኩኩሉ በልልኝ፡፡" አለው፡፡ አውራ ዶሮውም "እሺ!" አለውና እንደገና "ኩኩሉ…" ለማለት ዐይኑን ጨፍኖ ጎንበስ አለ፡፡ አውራ ዶሮው ባጎነበሰበት ቅጽበት ቀበሮው ቶሎ ዘሎ አውራ ዶሮውን ያዘና ወደጫካ ሮጠ፡፡ እረኞች ደግሞ የቀበሮውን **ድርጊት** በርቀት ሆነው ስለተመለከቱ እየ**ተጣደፉ** ይከተሉት ጀመር፡፡

## …ተማሪዎች ዶሮው ከተኩላው የሚያመልጥ ይመስላችኋል?…

ቀበሮው ፍጥነቱን በመጨመር አውራ ዶሮውን በአፉ ይዞ ወደፊት **ፈረጠጠ**፡፡ እረኞቹም በተመሳሳይ ፍጥነታቸውን በመጨመር ተከተሉት፡፡ በዚህ ጊዜ አውራ ዶሮው ቀበሮውን "የሚከተሉህ ሰዎች እንዳይገድሉህ የያዝኩት ዶሮ የናንተ አይደለም በላቸው፡፡" አለው፡፡ ቀበሮውም ዶሮው የነገረውን ለእረኞቹ ለመናገር አፉን ሲከፍት ዶሮው ወደእረኞቹ ሮጠ፡፡ እረኞቹም ዶሮውን ይዘው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ ዶሮው በቀበሮው **ብልሀት** ቢታለልም የቀበሮውን ብልሀት ለራሱም ስለተጠቀመበት ከመበላት ዳነ::

# አዳምጦ መናገር

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች የምንባቡን አንኳር ነጥብ ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ የሰጡትን ምላሽ መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪው መፅሃፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን መሰረት አድርገው በመማሪያ መፅሃፉ ላይ የቀረቡትን በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች ያሰሩዋቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡-**

- ✓ የጥያቄዎቹ መልሶች እንደተማሪዎቹ የግናዛቤ ሁኔታ ስለሚለያይ እርስዎ የጋራ የሆነ ግንዛቤ እንዲይዙ ምላሽ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ያዳመጡትን ተረት በማስታወስ ተራ በተራ እየተነሱ በቃል እንዲናገሩ አድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን ተረቶች እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በተረቱ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን አንኳር ነጥብ በአጭሩ ይግለፁላቸው፡፡

🗝 ቃላ

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች የማዛመዱን ጥያቄ ከመስራታቸው በፊት ከምንባቡ ውስጥ ሁለት ቃላትን በማውጣት እንዴት በምንባቡ መሰረት ፍቺ እንደሚሰጥ ያሳዩዋቸው፡፡
- ✓ **ቃላት** በሚለው ተግባር ስር ያለውን ማዛመድ በምንባቡ መሰረት ለቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

**መልስ**

1. ሠ
2. ሐ
3. ለ
4. መ
5. ሀ

**መምህር፡-**

- ✓ ተነጣጥለው የተቀመጡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት በማጣመር እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ✓ ተጨማሪ የተነጣጠሉ ቃላትን ለተማሪዎቹ በመስጠት በቡድን ሆነው እንዲያጣምሯቸው በማድረግ ተግባሩን በአግባ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

**መልስ፡-** 1. ጀመረች

2. አፉን

3. ቀበሮው

4. ወደጫካ

5. ለመናገር

- ✓ በትዕዛዝ ፪ ላይ ተጣምረው የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት እየነጣጠሉ እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ በዚህ መልኩ እርማት ይስጧቸው፡-

**መልስ፡-** 1. ቅርስ-ኦች

2. በሬ-ዎች

3. መፅሃፍ-ኦች

4. ደብተር-ኦች

## አንብቦ መረዳት

**መምህር፡-**

- ✓ የዕለቱን ትምህርት ያስተዋውቁ፡፡
- ✓ ከምንባቡ በፊት የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ከ3-7 ባለው ደቂቃ ውስጥ ያሰሯቸው፤ተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልሶችና ግምቶች የተወሰኑትን በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት የጎበኟቸውን ቅርሶች መገኛ ቦታቸውን ጭምር ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረበውን ምንባብ ሁሉም ተማሪዎች በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፤ በመቀጠል የምንባቡን አንቀፅ ለተማሪዎቹ በማከፋፈል ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች አንብበው ከጨረሱ በኋላ ያበረታቷቸው፡፡

## ቃላት

መምህር፦

- ✓ ለቃላት ፍቺ የምንሰጥባቸው መንገዶች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል የቃላት ተቃራኒ ፍቺ አንዱ ነው፡፡ የተወሰኑ ቃላትን በምሳሌነት በመስጠት እንዴት ተቃራኒ ፍቺ እንደሚፈልጉ ያሳዩዋቸው፡፡
- ✓ በመቀጠል የቀረበውን ተግባር በግል እንዲሰሩ ያድርጉ፤ እርማት ይስጧቸው፡፡

  መልስ፦ 1. ጥቂት
  2. ጥላቻ
  3. ጦርነት
  4. ገጠር
  5. ዘንድሮ

መምህር፦

- ✓ ተማሪዎች አንብበው ከጨረሱ በኋላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡
- ✓ በምንባቡ መሰረት ለጥያቄዎቹ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ከላይ ካነበቡት ምንባብ ውስጥ የተረዱትን ሐሳብ ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ፤እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባራቱን ሲያሰሩ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ታሳቢ ያድርጉ፡፡

መምህር፡-

- ✓ ስለ ባለ አራት ፊደል ቃላት አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
  ባለ አራት ፊደል ቃል ማለት  በአራት ፊደላት የተዋቀረ ቃል ነው፤ ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- ✓ "እናስተዋውቃችሁ" በሚል ርዕስ ካነበቡት ምንባብ ላይ ባለ አራት ፊደል ቃላትን ለይተው እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

**መምህር፡-**

- ✓ ተግባሩን ሲሰሩ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር የሚያቀርቡትን ይዘት እነሱን ባማከለ መልኩ ይቅረጹ፤ ሌሎች ልዩ ፍላጎት የሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እንደሁኔታው አካተው ያሰሯቸው፡፡
- ✓ **መልስ፡- ፩.**
  1. እንጠጦ
  2. ህብረት
  3. የካቲት
  4. በርካታ
  5. ሃውልት

  (ሌሎችም ቃላት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡)
- ✓ **መልስ፡- ፪.**
  1. ተረት
  2. ቅሪት
  3. ቅርስ
  4. ተስፋ
  5. በረታ
- ✓ **መልስ፡- ፫.** ከላይ የመሰረቷቸውን ቃላት ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩባቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ ከላይ ካለው ተግባር ጋር ተዛማጅነት ያለው የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

መምህር፡-

- ✓ የምዕራፉን አንኳር ነጥቦች በአጭሩ ይከልሱላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች 5 አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፤ ከዚያም የማጠቃለያ መልመጃዎችን ቡድን ሆነው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የሰሯቸውን የሥርዓተ ነጥብ ጽሑፎች በሚገባ በመገምገም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የማጠቃለያ መልመጃውን ያሰሯቸው፤ በሚከተለው መልኩ እርማትም ይስጧቸው፡፡

መልስ፡-

| ባለ 2 ፊደል | ባለ 3 ፊደል | ባለ 4 ፊደል |
|---|---|---|
| ሰራ | አሰራ | ወንበር |
| ፈራ | ሰራች | አበደረ |
| ደራ | በለጠ | አጣራች |
| ጣረ | ባለጌ | ወሰደች |
| ሰጠ | ጠለፈ | ተራበች |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “አውራ ዶሮና ቀበሮ” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ ባለአራት ሆሄ ቃላትን እንዲለዩ፣ የቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲፈልጉ፤ በፊደላት ቃላትን እንዲያዋቅሩ፤ ቃላትን ከብዙ ቁጥር ወደነጠላ ቁጥር እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ “አዲስ አበባ” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ በተጨማሪም በአራት ነጥብ፣ በጥያቄ ምልክትና በቃለአጋኖ ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉና በፅሁፍን እንዲያሚሉ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪዎች መጽሐፍ የማጠቃለያ ተግባራት ቀርበዋል፡፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አራት

# የአትክልት ቦታ

18

ክፍለ ጊዜ

## ➢ የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ከዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ልዩ የሆነውን ሀሳብ ታወጣላችሁ፡፡
- ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ትለያላችሁ፡፡
- በነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ ታስገባላችሁ፡፡

## ➢ የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- ፅህፈት

## ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- ✓ የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከ5-7 ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ያሉ የአትክልት ቦታዎችን ወይም መናፈሻዎችን እንዲዘረዝሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ የአትክልት ቦታዎችና የመናፈሻዎችን ጥቅም በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ✓ ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡
- ✓ እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

ወሩ ካቲት ነው፡፡ የአንደኛው መንፈቀ አመት ትምህርት ተጠናቆ የሁለተኛው መንፈቀ አመት የተጀመረበት እለት ነው፡፡ ረፍት ሲደወል ሮቤልና ዋእኒና የአንደኛው መንፈቀ አመት የረፍት ጊዜያቸውን እንዴት እንዳሳለፉ ማውራት ጀመሩ፡፡ ሮቤል ለዋእኒና "ብታይ ዋእኒና ጥሩ ውጤት በማምጣቴ እናቴ ልብስ፣ ጫማ፣ የተረት መጽሐፍ ገዝታ ሸለመችኝ፡፡ አባቴ ደግሞ (አያቶ ወደ ሚኖሩበተረ ሆሳዕና ወሰደኝ ከአያቶቼ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፤አባቴ አጎቴን ልጄን ወደ መዝናኛ ስፍራ ውሰደው አለው ፡አጎቴም እሺ በጣም የሚያምሩ የመዝናኛ ስፍራዎች አሉ፡፡ግን የትኛው እንደሚሻል እየዞርን እናያለን፡፡ጎፈር ሜዳም አሳ ማምረት ጀምሯል፡፡የመዝናኛ ስፍራውም ባማረ ባማረ ሁኔታ እየተሰራ ነው ሲል ማስታወሻ እየያዝኩ ነበር፡፡አጎቴም ስለቦታው ማብራራቱን ቀጠለ፡፡የወጣቶች መዝናኛ እና ስፖርት ሆቴልም ዘመናዊ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል እያለ ማብራራቱን ቀጠለ ፡-የጎፈር ሜዳ መናፈሻም ወጣቶች በመደራጀት አሳምረውት አሳ ያመርታሉ ፣የመዝናኛ ፡-ለሰርግ፣ለልደትና ለልዩ ልዩ ዝግጅቶችም አገልግሎት ይሰጣል፡፡ወጣቱም የእረፍት ጊዜውን በነፋሻማውና በጽዱው ጎፈር ሜዳ ሐይቅ ያሳልፋሉ፡፡በማለት ማባራሪያ ሰጠ፡፡ብቻ ዋእኒና ቦታው እንዴት እንደሚያምር በማለት ነገረው ዋእኒናም በሰማው ነገር በጣም በመጓጓት ይህ መናፈሻ የት ነው የሚገኘው በማለት ጠየቀው፤ሮቤልም ሆሳዕና ከአደባባይ ወደ ማርያም በር ስትደር ደወ ግራ በመታጠፍ ትንሽ ወረድ እንዳሉ ከዋቸሞ ትምህርት ቤት በስተቀኝ

**መሳይ ለማ ከጉዞ ማስታወሻ የተወሰደ ጥቅምት**

## አዳምጦ መናገር

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች የምንባቡን አንኳር ነጥብ ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፡፡
- ✓ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ✓ በማዳመጥ ተግባሩ በተጠበቀው የብቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱ ተማሪዎች ካሉ ክፍተቱን ለመሸፈን የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የማዳመጥ ተግባርን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

**መምህር፡-**

- ✓ የማዛመድ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ተግባር (ስዕሎችን ከመግለጫቸው ጋር) እንዲያዛምዱ ያድርጉ፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡፡

- ✓ ስዕሎችን በቃላት በመግለጽ ሲያሰሩ ሌሎች የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ካሉ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ያግዟቸው፡፡

**የስዕል ማዛመድ ተግባር መልስ**

1. ሐ
2. ሀ
3. መ
4. ሠ
5. ለ

- ✓ በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ስዕሉን በሚገባ ያብራሩላቸው፤ ምላሻቸውን በቃል ይቀበሏቸው፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡፡

## ሠ☞ መነጠልና ማጣመር

**ተግባር ፩**

**መምህር፡-**

- ✓ መነጠልና ማጣመርን በተመለከት ምንነቱንና ጠቀሜታውን ለተማሪዎች ይከልሱላቸው፡፡
- ✓ ለተማሪዎቹ የሚከተሉትን ቃላት አንብቡላቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ሰበሰበ | ዶማ |
| ረዘመ | ቀጠቀጠ |
| ሰላጣ | ደለበ |

- ✓ ተማሪዎቹ ያነበቡላቸውን ቃላት በትክክል መጻፋቸውን እየዞሩ ደብተራቸውን በማየት ያረጋግጡ፡፡
- ✓ የጻፏቸውን ቃላት የመጀመሪያ ፊደላት እንዲያጠፉና እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በፃፉትን ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን ቦታ እንዲያቀያይሩና ሌላ አንድ ፊደል በመጨመር ሌላ ቃል እንዲመሰርቱ ያበረቷቷቸው፡፡
- ✓ ለተማሪዎች አሰራሩ ግልጽ ይሆንላቸው ዘንድ በርካታ ምሳሌዎችን ቀድመው ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ተግባሩን ለመተግበር የሚቸገሩ ከሆነ ከተሰጡ ቃላት የመጀመሪያ ፊደሎችን ለይቶ የሚያሳይ ቻርት አዘጋጅተው ለሁሉም ተማሪዎች የሚታይ ቦታ ላይ ያስቀምጡት፡፡

## የተግባር ፩ መልስ

| የተሰጠ ቃል | ቦታ ሲቀያየሩ | ምስርት ቃል |
|---|---|---|
| ሰበሰበ = | በሰበሰ | በሰበሰች |
| ረዘመ = | መረዘ | ተመረዘ |
| ሰላጣ = | ላሰጣ | ላሰጣው |
| ዶማ = | ማዶ | የማዶ |
| ቀጠቀጠ= | ጠቀጠቀ | ጠቀጠቀው |
| ደለበ = | ደለበ | የደለበ |

(የተግባር አንድ ምላሾች ከላይ የተጠቀሱት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች አማራች ምላሾችም ሊኖሯቸው ይችላል፡፡)

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**በተግባር ሁለት ላይ ተነጣጥነውና ተጣምረው የቀረቡ ቃላትን ነጣጥለውና አጣምረው እንዲያነቡ ያግዟቸው፡፡

- ✓ ተማሪዎች ተግባሩን በሚገባ እንዲያከናውኑት ከተግባራቱ ውስጥ የመጀመሪያውን በምሳሌነት ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በትክክል መሥራታቸውን ለመመዘን ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡-**

- ✓ ከምንባቡ በፊት የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ከ3-5 ባለው ደቂቃ ውስጥ ያሰሯቸው፤ ተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልሶችና ግምቶች የተወሰኑትን በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች "አባማው ግቢ" የሚለውን ምንባብ በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡-**

- ✓ የንባቡ ሂደት ሲጠናቀቅም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ባማከለ መልኩ በጽሁፍ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች "አበባማው ግቢ" ከሚለውን ምንባብ ምን እንደተማሩ በጋራ እንዲወያዩ፡-
  - አምስት አባላት ያሉት ቡድን ይመስርቱ፡፡
  - የቡድን አወያያ (መሪ) እዲመርጡ ያድርጉ፡፡
  - የቡድን አባላቱ ከምንባቡ የተማሩትን በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡
  - የቡድናቸውን ሀሳብ በጽሑፍ እንዲያቀርቡት ያድርጉ፡፡
  - ሁሉም ቡድኖች በታዘዙት መልኩ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡
  - ከዚያም ከቡድን አባላቱ መካከል አንድ ተማሪ በጽሁፍ ያዘጋጁትን የቡድኑን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡ ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ከገለጹ በኋላ እርስዎ ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች በነጠላ ቁጥር የቀረቡትን ቃላት ወደ ብዙ ቁጥር በመቀየር እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ✓ አሰራሩ ግልጽ እንዲሆን በርከት ያሉ ምሳሌዎችን ቀድመው ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው፡፡

  - ✓ የዕለቱን ትምህርት ተማሪዎች በሚገባ መተግበራቸውን ለመመዘን ተጨማሪ ቃላትን አዘጋጅተው የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች በተዘረዘሩላቸው ፊደላት የሚመሰረቱ ቃላትን ከሳጥኑ ውስጥ በመምረጥ  በፊደላቱ ጎን ቃላቱን እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በተባሉት መንገድ መስራታቸውን ለማረጋገጥ በመማሪያ ክፍሉ እየተዘዋወሩ ቅኝት ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎች   ቃላትን ከሆሄዎች ጋር በየግላቸው እንዲያዛምዱ ካደረጉ በኋላ የሰሩትን በማየት ግብረ-መልስ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም እርስዎ የሰሯቸውን መልሶች ለተማሪዎች ንገሯቸው፡፡

## ተግባር ፪

- ✓ በተግባር ፪ ላይ ያሉ ምስሎችን በትኩረት በመመልከት ስማቸውን በክፍት ቦታው ላይ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ የሰጧውን ምላሾች በመመልከት የተሳሳቱ ተማሪዎች ካሉ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

- ✓ ተማሪዎች በክቡ ውስጥ በተዘረዘሩላቸው ፊደላት ቃላት እንዲመሰርቱባቸው ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌዎቹን እንዲያ ያድርጓቸው፤ ግልፅ ካልሆነላቸው አሰራሩን ያሳዩዋቸው፡፡

- ✓ ተግባሩን በተባሉት መንገድ መስራታቸውን ለማረጋገጥ በመማሪያ ክፍሉ እየተዘዋወሩ የጻፏቸውን ቃላት ይመልከቱላቸው፡፡
- ✓ የቃላት ምስረታውን ተግባር ተማሪዎች በግል ከሰሩ በኋላ የሰሯቸውን መልሶች ተማሪዎች እንዲናገሩ ያድርጉና ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ፈጣን ተማሪዎችን ለመደገፍ ሌላ ተመሳሳይ ተግባር አዘጋጅተው እንዲተገብሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ፈጣን ተማሪዎችን ለመደገፍ ሌላ ተመሳሳይ ተግባር አዘጋጅተው እንዲተገብሩ ያድርጉ፡፡

**የተግባር፲ ናሙና መልስ**

1. መኮትኮቻ
2. አንድነት
3. አካፋዎች
4. አከናወነ
5. አተካከል
6. ተከለከለ …

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ "አበባማው ግቢ" በሚል ርዕስ ስር ለአንብቦ መረዳት ተግባር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እየደጋገሙ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳየት አንድ አጠር ያለ ጽሑፍ መርጠው ወይም አዘጋጅተው በጥሩ የአነባበብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ ባለፉት ምዕራፎች አቀላጥፈው ያላነበቡ ተማሪዎችን በመለየት ቆመው ድምፅ በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻቸው ደቂቃ እየመዘገቡ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ (ደቂቃውን እርስዎ ይያዙላቸው)
- ✓ አቀላጥፎ ማንበብን ሲተገብሩ በእርስዎ መንገድ የተለያዩ መተግበሪያ ስልቶችን ቢተገብሩ ይበረታታል፡፡
- ✓ በአቀላጥፎ ማንበብ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን እርስ በእርስ የሚተራረሙበትን አውድ ያመቻቹላቸው፡፡
- ✓ ዐይነ ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ የሚያነቡትን ጽሑፍ በብሬል እንዲጻፍላቸው ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር አብረው ይሥሩ፡፡

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በአቀላጥፎ ማንበብ ስር በትዕዛዝ ፪ ያለውን ተግባር ለተማሪዎቹ ያሳሯቸው፡፡
  - አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክትና ቃለ አጋኖ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ምን አይነት ድምጸት ሊኖር እንደሚችል ተማሪዎችን ያስረዷቸው፡፡
  - ሀሳቡ የበለጠ የተብራራ ይሆን ዘንድ የተለያዩ አስረጂዎችን በመጠቀም ያስረዷቸው፡፡
  - ከዚያም በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት በተግባር ሁለት የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ዓረፍተ ነገሮቹን የተለያዩ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ እጅ የማያወጡ (ለማንበብ ፍቃደኛ ያልሆኑ) ተማሪዎች ካሉም እነሱም እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ የአነባበባቸውን ትክክለኛነት አስመልክቶ እርማት  ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

### በቃላት ዓረፍተ ነገር መመስረት

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች በቃላት ዓረፍተ ነገር በማፍለቅ እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ለየብቻቸው እንዲሠሩት ያድርጉ፡፡
- ✓ የሠሩትን ዓረፍተ ነገር የብጤ እርማት እንዲሠጡበት ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ተማሪዎች ለሰሠሩት ተግባር እርማትይስጧቸው፡

### ሥርዓተ ነጥብ

- ✓ የአራት ነጥብና የጥያቄ ምልክትን አጠቃቀም በተመለከተ ባለፉት ምዕራፎች የተማሩትን ይዘት ከአሁኑ ይዘት ጋር ለማዛመድ እንዲመች ይከልሱላቸው፡፡
- ✓ ስለቃለአጋኖ አጠቃቀም ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይስጧቸው፤ ማብራሪያውን በበቂ አስረጅዎች ያስደግፉ፡፡
- ✓ አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክት እና ቃለ አጋኖን የሚገልጽ ምልክት እና ስማቸውን የሚያሳይ ቻርት በመርጃ መሳሪያነት ይጠቀሙ፡፡
- ✓ ከክለሳውና ከገለጻው በኋላ ቃለአጋኖን በመጠቀም ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ✓ የጻፉትን ዓረፍተ ነገር ከሥርዓተ ነጥቦች ጋር በማዛመድ መጻፋቸውን ይመልከቱ፡፡

## ታሪክ መጻፍ

- ✓ ታሪክ ለመጻፍ እንደመነሻነት እንዲጠቀሙት የቀረበውን አንቀጽ በአንክሮ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ✓ ጽሑፉን ሲያነቡ ትኩረት ማድረግ ያለባቸውን ጉዳዮች ቀድመው ይንገሯቸው፡፡
- ✓ ታሪክ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው በቡድን ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹላቸው፡፡
- ✓ ከዚያም ከቤተሰቦቻው ወይም ከሚያውቋቸው ሰዎች አንዳቸውን በመምረጥ ባነበቡት ጽሁፍ መሰረት የህይወት ታሪካቸውን የግል እንዲጽፉ የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በግል የጻፏቸውን ታሪኮች በቡድን ሆነው ካዩዋቸው በኋላ አንዱን የተሸለ አጻጻፍ የተከተለውን ታሪክ እንዲመርጡና እንደገና አሻሽለው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡
- ✓ በየቡድኑ እየተዘዋወሩ ያግዟቸው፤ይምሯቸው፡፡
- ✓ የጻፉትን ታሪክም በማየት እርማት ይስጧቸው፡፡

## የቃላት ፍቺ

- ✓ "የማዕዶት አኅት" የሚለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጽሐፉ ለተዘረዘሩ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ለተግባራቱም በቂ ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

## የተግባሩ መልስ

ሀ. ትጉ          መ. በቀጣይ

ለ. ስፍራ          ሠ. ስራውን

ሐ. በርትቶ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “የማርታ ማስታወሻ” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ ስዕላዊ መግለጫዎችን በቃላት መግለፅ፤ ቃላትን በመነጠልና በማጣመር እንዲፅፉ፤ የፊደላትን ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላትን እንዲያዋቅሩ ተደርጓል፡፡ “አበባማው ግቢ” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ በተጨማሪም በአራት ነጥብ፤ በጥያቄ ምልክትና በቃል አጋኖ የተጻፈ ፅሁፉን እንዲያነቡ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪ መጽሐፍ ላይ የማጠቃለያ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ በተማሪ መጽሃፍ ላይ የተቀመጠውን የክለሳ ጥያቄዎች ያሰሯቸው በአግባቡ መስራታቸውን በመከታተል ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

አማርኛ

፩ኛ ክፍል

ምዕራፍ አምስት

# የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ

18

ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

- ካዳመጡት ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ልዩ የሆነውን ሀሳብ ያወጣሉ፡፡
- ቃለ አጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ፡፡
- በነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ ያስገባሉ፡፡

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- ፅህፈት

## ማዳመጥ

### መምህር፡-

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከ5-7 ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

### የጤና ቁልፍ

ሁሉም ልጆች አባባ ምትኩ ጋር ለመሄድ ተጣድፈዋል፡፡ እንደምንም ብለው በሚገናኙበት ሰዓት አባባ ጋር ደረሱ፡፡ አባባም ልጆችዬ እንዴት አደራችሁ? ሰላም ናችሁ? በማለት ሰላምታ ሰጡ፡፡ ልጆቹም ደህና መሆናቸውን ገለፁላቸው፡፡ አባባም ተረታችውን ለማውራት የልጆቹን ሁኔታ መመልከት ጀምሩ፡፡ ሁሉም ልጆች ከሌላ ቀናቸው ለየት ብለው አዩዋቸው፡፡ የተወሰኑት ጸጉራቸው ተንጨብርሯል፤ የተወሰኑት ደግሞ ልብሳቸው ቆሽሿል፡፡ አባባም ሊያወሩት ያሰቡትን ተረት ትተው ወደ ምክር ገቡ፡፡

“ልጆችዬ "ጤና ለሰው ልጅ ወሳኝ ነው፡፡ የሰው ልጆች ጤና ከሌለን በህይወት መኖር አንችልም፡፡ መማር፣ መስራትና ያሰብንበት ቦታ ለመድረስ ይከብደናል፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ጤናችንን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡”

## ተማሪዎች ጤነኛ ለመሆን ምን ምን ማድረግ አለብን?

ጤናማ ለመሆን ደግሞ የግልና የአካባቢችንን ንፅህና መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡በግላችን ልብሳችንን "ማጠብ፣ ሰውነታችንን መታጠብ፣ ፀጉራችንን መታጠብና ማበጠር፣ ጥርሳችንን መፋቅ እንዲሁም ጥፍራችንን መቁረጥ ይገባል፡፡ ይህንን ብቻ በማድረግ ደግሞ የተሟላ ጤናን ማግኘት አይቻልም፤ ስለዚህ በጋራ አካባቢያችንን ዘወትር በጋራ በመሆን ማፅዳትና መንከባከብ አለብን፡፡ ሌላው የምንጠጣውን ውኃ በማፍላት፤ የሕመም ስሜት ሲሰማን በመታከም ጤናችንን እንጠብቅ፡፡ በአጠቃላይ የጤናችን ቁልፍ ንጽሕህና ስለሆነ ንጽህናችን በመጠበቅ ጤናችን እንጠብቅ፡፡" ብለው ለልጆቹ ምክራቸውን ለገሱ፡፡

**መምህር፡-**

- ❖ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፡፡
- ❖ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ❖ በማዳመጥ ተግባሩ በተጠበቀው የብቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱ ተማሪዎች ካሉ ክፍተቱን ለመሸፈን የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የማዳመጥ ተግባርን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

🗝 ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ የማዛመድ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያሉትን የማዛመድ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፩ መልስ

| | |
|---|---|
| 1. ሰ | 4. መ |
| 2. ሠ | 5. ሐ |
| 3. ሀ | 6. ለ |

### ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ የተዘረዘሩ ቃላት የያዙትን ፊደላት ቦታ በማቀያየር ሌሎች ቃላትን እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ለማቅለል ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ያሰሯቸው፡፡
- ✓ የሚመሰርቷቸው ቃላት የፊደል ብዛታቸው ስላልተወሰነ በአንዱ ቃል በርከት ያሉ ምሳሌዎችን እንዲያፈልቁ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በታዘዙት መልኩ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተግባሩን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው እንደጨረሱም የሰሩትን ሥራ ይዩላቸውና ለተሳሳቱ ተማሪዎች ማስተካከያ ይስጡ፤ ተማሪዎች ከጠቀሷቸው ውጭ ሌሎች ቃላት መመስረት ከቻሉ ይቀበሏቸው፡፡

☞ **መነጠልና ማጣመር**

**ተግባር ፩**

**መምህር፡-**

- ✓ መነጠልና ማጣመርን በተመለከት ምንነቱንና ጠቀሜታውን ለተማሪዎች ይከልሱላቸው፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለማጣመር ተግባር ተነጣጥለው የቀረቡ ቃላትን አጣምረው እንዲጽፉና እዲያነቡ ያድርጉ፡፡
  - በመጀመሪያ በቂ ምሳሌዎችን በመለማመጃነት ያሰሯቸው፡፡
  - ከዚያም በመማሪያ መጽሐፉ ትዕዛዝ ፩ ላይ ተነጣጥለው የተጻፉ ቃላትን አጣምረው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
  - ከዚያ ሁለት ሁለት ተማሪዎችን በየተራ እያስነሱ አንደኛው ተማሪ ከመማሪያ መጽሐፉ ተነጣጥለው የተጻፉትን ሲያነብ ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ተጣምረው የተጻፉ ቃላትን እንዲያነብ ያድርጉ፡፡
  - ነጣጥለውና አጣምረው ሲያነቡ የሚኖሩ ስህተቶችን በመመልከት ቃላዊ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን ለማበልጸግ በመርጃ መሳሪያነት ስዕል፣ የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ጥቁር ሰሌዳ … እንዳስፈላጊነቱና እንደመማሪያ ክፍሉ አመችነት በመምረጥ ይጠቀሙ፡፡

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በተግባር ፪ ላይ በአዎንታዊ ቅርጽ የቀረቡ ቃላትን ወደአሉታዊ ቅርጽ የሚቀይር ቅጥያ በመጨመር እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
    - ተማሪዎች ተግባሩን በሚገባ እንዲያከናውኑት ከተግባራቱ ውስጥ የመጀመሪያውን በምሳሌነት ያንብቡላቸው፡፡
    - ከዚያም መጀመሪያ በአዎንታዊ ቅርጽ ከቀረቡትን ቃላት ላይ /አል-/ን መጀመሪያ ላይ "-ም"ን ደግሞ መጨረሻ ላይ እንዲቀጥሉ ያግዟቸው፡፡
    - በመቀጠል የተነጣጡትን ቃላት እንዲያነቧቸው እድል ይስጧቸው፡፡
    - በመጨረሻም ቅጥያዎችን ከቃላቱ ጋር አጣምረው እንዲያነቧቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ ተግባሩን በትክክል መሥራታቸውን ለመመዘን ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## ንባብ

### "ታሞ ከመማቀቅ..."

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን "ታሞ ከመማቀቅ" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ግለንባባቸውን ሲጨርሱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፪

❖ ተማሪዎች “ታሞ ከመማቀቅ…” የሚለውን ምንባብ መልዕክት እንዲለዩ በጋራ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች ሶስት ወይም አራት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አወያያ (መሪ) እዲመርጡ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አባላቱ የምንባቡ መልዕክት በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡
- የቡድናቸውን ሀሳብ በሁለት ዓረፍተ ነገር ጠቅለል አድርገው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች በታዘዙት መልኩ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡

- ከዚያም ከቡድን አባላቱ መካከል አንድ ተማሪ እርስዎ መርጠው በጽሁፍ ያዘጋጁትን የቡድኑን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡ ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ከገለጹ በኋላ እርስዎ ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፩ መልስ

1. ለ　　3. ሐ

2. ሐ　　4. ለ

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- "ታሞ ከመማቀቅ..." በሚል ርዕስ ስር ለአንብቦ መረዳት ተግባር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እየደጋገሙ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳየት የተመረጠውን ምንባብ አንድ ጊዜ በጥሩ የአነባበብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡
- ባለፉት ምዕራፎች አቀላጥፈው ያላነበቡ ተማሪዎችን በመለየት ቆመው ድምፅ በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻቸው ደቂቃ እየመዘገቡ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ (ደቂቃውን እርስዎ ይያዙላቸው)
- መጀመሪያ የሚያነቡትንና መጨረሻ ላይ የሚያነቡትን በመገምገሚያና በመከታተያ ቅጽ መዝግበው እገዛ ለሚያስፈልጋቸው እገዛ ይስጡ፡፡
- ተግባሩን ሲያስተገብሩ በመከታተያና በመገምገሚያው ቅጽ መሰረት ግብረመልስ ይስጡ፡፡

| | መስፈርቶች | የመጀመሪያ ንባብ | ሁለተኛ ንባብ |
|---|---|---|---|
| | | (/) | (/) |
| ሀ | በትክክል ያልተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ለ | ተቆራርጠው የተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ሐ | በትክክለኛ ድምጸት ያልተነበቡ ሥርዓተ ነጥቦች ብዛት | | |
| መ | በአንድ ደቂቃ ውስጥ የተነበቡ ቃላት ብዛት | | |

- ከላይ ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀውን የትግበራ መከታተያና መገምገሚያ ቅጽ እንዳስፈላጊነቱ ይጠቀሙበት፡፡
- ተማሪዎችም እርስበርስ የብጤ እርማት ይሰጣጡበት ዘንድ በቻርት አዘጋጅተው ለተማሪዎች የሚታይ ቦታ ላይ ያድርጉላቸው፡፡

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በአቀላጥፎ ማንበብ ስር በትዕዛዝ ፪ ያለውን ተግባር ለተማሪዎቹ ያሰሯቸው፡፡
  - አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክትና ቃለ አጋኖ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ምን አይነት ድምጸት ሊኖር እንደሚችል ተማሪዎችን ይከልሱላቸው፡፡
  - ሀሳቡ የበለጠ የተብራራ ይሆን ዘንድ የተለያዩ አስረጂዎችን በመጠቀም ያስረዷቸው፡፡
  - ከዚያም በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት በተግባር ሁለት የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ዓረፍተ ነገሮቹን የተለያዩ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ በመገምገሚያው መስፈርት መሰረት እርስበርስ
- ✓ የአነባበባቸውን ትክክለኛነት አስመልክቶ እርማት  ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ዐይነ ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ የሚያነቡትን ጽሑፍ በብሬል እንዲጻፍላቸው ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር አብረው ይሥሩ፡፡

## 🗝 ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ስለተቃራኒ ፍቺ ማብራሪያና ምሳሌ ከሰጡ በኋላ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያለውን ተግባር የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባሩ ፩ መልስ**

| | |
|---|---|
| 4. ሠ | 4. ለ |
| 5. ሀ | 5. ሐ |
| 6. መ | |

### ተግባር ፪

- ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ቃላትን ከዓረፍተ ነገሮች ጋር እንዴት ማዛመድ እንዳለባቸው ያስረዷቸው፡፡
- በትዕዛዝ ፪ ላይ ያለውን ቃላትን ከዓረፍተ ነገሮች ጋር የማዛመድ ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- በመቀጠል ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው፡፡

### ተግባር ፫

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፫ ላይ በስዕል የቀረቡትን ከንጽህና ጋር የተያያዙ አገላለጾችን መረዳት ይችሉ ዘንድ ምሳሌውን ያብራሩላቸው፡፡
- ከዚያም ተግባሩን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣... ይጠቀሙ፡፡

## ተግባር ፬

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፬ ላይ ያልተሟሉ ቃላትን (የተጓደሉ ሆህያትን ያሉባቸው ቃላትን) እንዲያሟሉ የሚያዝ ተግባር ቀርበዃል፡፡ ተግባሩን ሳይቸገሩ መስራት ይችሉ ዘንድ ምሳሌውን ያብራሩላቸው፡፡
- በምሳሌው መሰረት ተግባሩን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ካሉ ተግባሩ እነሱን ያማክል ዘንድ እንደሁኔታው እርዳታ ያድርጉላቸው፡፡
- ተግባራቱን ሲሰሩ ክትትል ያድርጉላቸው፡፡
- በመጨረሻም እርማት ይስጧቸው፡፡

### ማጣመርና መነጠል

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፉ ተነጣጥለው የተጻፉ ቃላትን አጣምረው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ተነጣጥለውና ተጣምረው የተጻፉ ቃላትን ተራ በተራ እንዲያነቡና ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ሲያጣምሩም ሆነ ሲያነቡ የተፈጠሩ ስህተቶች ካሉ እርማት ይስጧቸው፡፡ በትክክል ካጣመሯቸውና ካጣመሯቸው ደግሞ ማበረታቻ ቃላትን ተጠቅመው ያበረታቷቸው፡፡

### ጽሕፈት

## የተጓደለ ዓረፍተ ነገርን ማሟላት

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች የተጓደሉ ዓረፍተ ነገሮችን በማሟላት እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ለየብቻቸው እንዲሠሩት ያድርጉ፡፡
- ✓ የሚያሟሏቸውን ዓረፍተ ነገሮች የብጤ እርማት እንዲሠጣጡበት ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ተማሪዎች ለሠሩት ተግባር እርማት ይስጧቸው፡፡

## የቃል ጽሕፈት

**መምህር፦**

- ✓ የሚከተሉትን ቃላት እያነበቡላቸው በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
  - ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በወረቀት ፅፈው ይስጧቸው፡፡

| | |
|---|---|
| • ፎጣ | ▪ ሶፍት |
| • በረኪና | • መወልወያ |
| • ሳሙና | • ውኃ |

- ✓ በትክክል መጻፋቸውን እየዞሩ ይከታተሏቸው፤ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

## ስርዓተ-ነጥብ

**መምህር፦**

- ✓ በትዕዛዝ ፫ ያሉ ዓረፍተ ነገሮችን አራት ነጥብ በመጨመር እንዲያሟሉ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተግባሩን በተናጥል እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ✓ በመርጃ መሳሪያነት የሥርዓተ ነጥቦችን ምልክት የያዘ ቻርት
- ✓ በመጨረሻም የብጤ እርማት እንዲሰጣጡ አድርገው ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ሲሰሩ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር የሚያቀርቡትን ይዘት እነሱን ባማከለ መልኩ ይቅረጹ፤ ሌሎች ልዩ ፍላጎት የሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እንደሁኔታው አካተው ያሰሯቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጤና ቁልፍ የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ “ታሞ ከመማቀቅ” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤የአንብቦ መረዳት፤የቃላት፤የማጣመርና የመነጠል፤የፅህፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት

# ባህላዊ ሙዚቃ

18

ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

- ፅሑፍን አዳምጠው  ተዘውታሪ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ
- ከሚነበብ ጽሑፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን በመለየት ፍቺ ይሰጣሉ
- የጥያቄ ምልክትንና ቃልአጋኖን ይጠቀማሉ
- ቃላትን ከመነሻ ቅጥያቸው ጋር አጣምረው ይጠራሉ።

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- ፅህፈት

## (((  ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከ3-5 ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- ከገመቷቸው ሀሳቦች መካከል የተወሰኑትን ይጻፏቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡
- ከሚያዳምጡት ምንባብ ውስጥ የተረዱትን ሃሳብ በሁለት አረፍተነገር እንዲገልጹ ይዘዟቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፤ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

### ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ኢትዮጵያ ብዙ የተለያዩ ባህሎች አሏት፡፡ከባህሎቿ አንዱ ባህላዊ ጭፈራ ነው፡፡ባህላዊ ጭፈራውን የሚያጅቡ ደግሞ በርከት ያሉ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪዎች አሉ፡፡ከባህል መሳሪዎች መካከል ማሲንቆ፣ ክራር፣ ዋሽንት፣ በገናና ከበሮ ይጠቀሳሉ፡፡

---

### ተማሪዎች ክራር ከምን ከምን የሚሰራ ይመስላችኋል?

---

**ማሲንቆ** ከእንጨትና ከፈረስ ጭራ የሚሰራ ባለአንድ አውታር(ክር) ነው፡፡ **ክራር** ከእንጨትና ከጅማት ክር አልፎ አልፎ ከቀጭን ሽቦ የሚዘጋጅ ነው፡፡ **ዋሽንት** ከሸንበቆ የሚሰራ እስከ ስድስት ሚደርሱ ቀዳዳዎች ያሉት የትንፋሽ መሳሪያ ነው፡፡ **በገና** ከበግ ወይም ከፍየል አንጀት እና ከእንጨት የሚሰራ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

እነዚህ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን በማጀብ ዜማቸው የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ ዜማቸውን ለማስተካከል ማሲንቆ፣ ክራር፣ በገና በእጅ ጣቶች የሚቃኙ ሲሆን ከበሮ በእጅ ይመታል፡፡ ዋሽንት ደግሞ በትንፋሽ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ባህላዊ ዘፈኑን በመምራት አገልግሎት ላይ የሚውሉት እነዚህ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች የአገር መለያና ቅርሶች ናቸው፡፡

**መምህር፡-**

- ❖ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፡፡
- ❖ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ❖ ተግባር ፪ን ለማሰራት የሚከተሉትን መንገዶች ይከተሉ፡፡
    - ከአራት እስከ ስድስት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡
    - የውይይቱን ሂደት እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
    - በቡድን ሆነው ሲወያዩ የቡድኑ አባላት በማዳመጡ ሂደት የጻፏቸውን ሀሳቦች መሰረት አድርገው እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
    - በቡድን ውይይቱ የተነሱ ሀሳቦችንና ያዳበጡትን ምንባብ ጠቅለል አድርገው በአንድ ላይ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
    - የጻፉትንም ጽሑፍ በማንበብ እርማት ይስጧቸው፡፡
- ❖ በማዳመጥ ተግባሩ በተጠበቀው የብቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱ ተማሪዎች ካሉ ክፍተቱን ለመሸፈን የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የማዳመጥ ተግባርን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

🗝 ቃላት

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ በስዕል የቀረቡትን የሙዚቃ መሳሪዎች ከስያሜያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ይዘዟቸው፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣… ይጠቀሙ፡፡
- ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡

## የተግባር ፩ መልስ

1. ለ
2. ሀ
3. መ
4. ሠ
5. ሐ

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ ያለውን ግጥም በትኩረት ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ከዚያም ጥንድ ጥንድ ሆነው በግጥሙ ውስጥ በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርሱ ቃላትን ለይተው እንዲያወጡ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ግልፅ ለማድረግ ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያብራሩላቸው፡፡

- ✓ በመጨረሻም በትክክል መስራት አለመስራታቸውን ለማረጋገጥ ደብተራቸውን በማየት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ደብተር ሲመለከቱ በርካታ ስህተቶችን የሰሩ ተማሪዎች ካሉ ይዘቱን ለማበልጸግ ቤታቸው ሰርተው የሚያመጡት ሌላ ተግባር ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

- ➢ ከማሰራትዎ በፊት ሆህያትን ከቃላት ጋር እንዴት ማዛመድ እንዳለባቸው ያስረዷቸው፡፡
- ➢ በትዕዛዝ ፫ ላይ ያለውን ቃላትን ከዓረፍተ ነገሮች ጋር የማዛመድ ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- ➢ በመቀጠል ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው፡፡

## ☞ መነጠልና ማጣመር

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ በቃል መጀመሪያ ላይ ሊመጡ ስለሚችሉ ቅጥያዎች በልጆቹ ደረጃ መጥነው ያስረዷቸው፡፡ የማብራሪያ ዓላማ ስለቅጥያዎቹ አይነትና አገልግሎት ማሳወቅ ሳይሆን መነጠል እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡
- ✓ ማብራሪያው ለተማሪዎቹ ግልጽ ይሆን ዘንድ በተለያዩ አስረጅዎች ይደገፍ፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለመነጠል ተግባር የቀረቡ ቃላትን ነጣጥለው እንዲጽፉና እዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ነጣጥለው የጻፏቸውን ለማንበብ ሁለት ሁለት ተማሪዎችን በየተራ እያስነሱ አንደኛው ተማሪ ከመማሪያ መጽሐፉ ተጣምረው የተጻፉትን ሲያነብ ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ተነጣጥለው የተጻፉ ቃላትን እንዲያነብ ያድርጉ፡፡
- ✓ ነጣጥለውና አጣምረው ሲያነቡ የሚኖሩ ስህተቶችን በመመልከት ቃላዊ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ እንዲሰሩ ለተማሪዎች ተጨማሪ ቃላቶችን ይስጧቸው፡፡ ለፈጣን ተማሪዎች ደግሞ የመጀመሪያና የመጨረሻ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት በመስጠት እንዲነጣጥሉና እንዲያጣምሩ ያግዟቸው፡፡

### የተግባር ፩ መልስ

1. ከ - እንጨት
2. የ - መሳሪያ
3. የ - ሚሰራ
4. ከ - ሸንበቆ
5. በ - ከብት

### ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ የተማሪዎችን ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ (ምልክቶችን የመረዳትና የመለየት ችሎታን) ለማሳደግ በትዕዛዝ ፪ ላይ ያለውን "እኔ ማን ነኝ?" የሚለውን ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- ✓ በትክክል ለመለሱ ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን ይጠቀሙ፤ ለተሳሳቱት ደግሞ እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ሄህያትን የመለየት ችሎታ በመመዘን የሚከብዷቸውን ሆህያት እንዲለዩ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፃችን፣ ካርቱኖችን፣... በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም ያለማምዷቸው፡፡

## 🕮 ንባብ

### የባህል ቀን

**መምህር፡-**

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን "የባህል ቀን" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ግለንባባቸውን ሲጨርሱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## 🗝 ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያለውን የማዛመድ ተግባር የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባሩ ፩ መልስ**

7. ሐ
8. ለ
9. ሀ

4. ሠ
5. መ

### ተግባር ፪

- ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩ ቃላትን እንዴት መመስረት እንደሚችሉ ያስረዷቸው፡፡
- የሚሠሩትን ተግባር ሳይቸገሩ ይተገብሩት ዘንድ ከተማሪ መጽሐፉ ካለው ምሳሌ በተጨማሪ ሌሎች ምሳሌዎችንም ይስጧቸው፡፡
- በትዕዛዝ ፪ ላይ ያለውን በተሰጧቸው ፊደላት መነሻነት ቃላትን እንዲመሰርቱ ያግዟቸው፡፡
- ተማሪዎቹ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ወቅት ምልከታ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠል ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፫ ላይ በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን የሙዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊና ዘመናዊ በማለት እንዲመድቡ ይዘዟቸው፡፡
- ተግባሩን የበለጠ ግልጽ እንዲሆንላቸው ምሳሌዎችን ቀድመው ይስጧቸው፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣... ይጠቀሙ፡፡
- ለሰሩት ተግባር ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፫ መልስ

| ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች | ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች |
|---|---|
| ከበሮ | ጊታር |
| ማሲንቆ | ሳክስፎን |
| ክራር | ፒያኖ |
| በገና | ማንዶሊን |
| ዋሽንት | ኪቦርድ |

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- **"የባህል ቀን"** በሚል ርዕስ ስር ለአንብቦ መረዳት ተግባር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እየደጋገሙ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳየት የተመረጠውን ምንባብ አንድ ጊዜ በጥሩ የአነባበብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡
- ባለፉት ምዕራፎች አቀላጥፈው ያላነበቡ ተማሪዎችን በመለየት ቆመው ድምፅ በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻቸው ደቂቃ እየመዘገቡ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ (ደቂቃውን እርስዎ ይያዙላቸው)
- መጀመሪያ የሚያነቡትንና መጨረሻ ላይ የሚያነቡትን በመገምገሚያና በመከታተያ ቅጽ መዝግበው እገዛ ለሚያስፈልጋቸው እገዛ ይስጡ፡፡
- ተግባሩን ሲያስተገብሩ በመከታተያና በመገምገሚያው ቅጽ መሰረት ግብረመልስ ይስጡ፡፡

| መስፈርቶች | | የመጀመሪያ ንባብ | ሁለተኛ ንባብ |
|---|---|---|---|
| | | (/) | (/) |
| ሀ | በትክክል ያልተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ለ | ተቆራርጠው የተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ሐ | በትክክለኛ ድምጸት ያልተነበቡ ሥርዓተ ነጥቦች ብዛት | | |
| መ | በአንድ ደቂቃ ውስጥ የተነበቡ ቃላት ብዛት | | |

- ➢ ከላይ ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀውን የትግበራ መከታተያና መገምገሚያ ቅጽ እንዳስፈላጊነቱ ይጠቀሙበት፡፡
- ➢ ተማሪዎችም እርስበርስ የብጤ እርማት ይሰጣጡበት ዘንድ በቻርት አዘጋጅተው ለተማሪዎች የሚታይ ቦታ ላይ ያድርጉላቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

### የቃል ጽሕፈት

**መምህር፡-**

- ✓ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮችን እያነበቡላቸው ተማሪዎቹ በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
    - ባህላዊ መሳሪያዎች ለሙዚቃ ያስፈልጋሉ፡፡
    - ሙዚቃ መንፈስን ያድሳል፡፡
- ✓ የጻፏቸውን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል መጻፋቸውን በመመልከት እርማት ይስጧቸው፡፡ ትምህርቱን ለማበልጸግም የተለያዩ የተቀረጹ ድምጾችን በመርጃ መሳሪያነት ያቅርቡላቸው፡፡

### ስርዓተ-ነጥብ

**መምህር፡-**

- ✓ በመርጃ መሳሪያነት የጥያቄ ምልክትና ቃል አጋኖን ሥርዓተ ነጥቦችን የያዘ ቻርትን/ ፍላሽ ካርድን ይጠቀሙ፡፡
- ✓ ትዕዛዝ ፪ ላይ ያለውን ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- ✓ የእርስ በርስ እርማት እንዲሰጣጡ አድርገው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

### ላወጡት ጥያቄ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት

- ✓ በትዕዛዝ ፫ የቀረቡትን ተግባራት በቡድን ሆነው እንዲሰሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ተማሪዎቹ ጥያቄዎች አውጥተው በጋራ በመሆን በፅሁፍ ምላሽ የሰጡበትን ተግባር ላይ ውይይት በማድረግ ማስተካከያ ሃሳብ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ሲሰሩ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር የሚያቀርቡትን ይዘት እነሱን ባማከለ መልኩ ይቅረጹ፤ ሌሎች ልዩ ፍላጎት የሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እንደሁኔታው አካተው ያሰሯቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "ትክክለኛ ዳኛ" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ "የስንፍና ጥግ" የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤የአንብቦ መረዳት፤የቃላት፤የማጣመርና የመነጠል፤የፅህፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ ተግባሮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

ምዕራፍ ሰባት

መልካም ስነ ምግባር

18

ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኂላ፡-

- ያዳመጡትን ፅሑፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ ዓ.ነገር ይመሰርታሉ
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ
- በተገቢ ፍጥነት አጫጭር ታሪኮችን ታነባላችሁ
- የተሰጣችሁን ቃላት በትክክል ይፅፋል

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ድምፅን የመገንዘብ ችሎታ
- ንባብ
- ፅህፈት
- ማፍለቅና መረዳት

## ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች በመገመቻ ቻርት ላይ እንዲያሰፍሩ ይዘዟቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡ በተጨማሪም ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላት ሲገጥሟቸው እንዲመዘግቡ ያድርጓቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

# ትክክለኛ ዳኛ

ፍርድ እንዳይጓደልበት አጥብቆ የሚጠነቀቅ አንድ እውነተኛ ዳኛ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ወዳጁ ከሰው ጋር ተጣልቶ ተከሰሰና ወደ እርሱ ዘንድ መጣ፡፡ ወዳጁ ወደፍርድ ቤት ከመሄዱ በፊት ከዳኛው ቤት ሄዶ እንዲህ አለው፡፡ “ከአቶ በልሁ ጋር ተካሰን ለሙግት አንተ ጋር መቅረባችን ነውና እንግዲህ የወዳጅነትህን ስራ እንድትሰራልኝ አደራህን፡፡” አለው፡፡

ዳኛው ግን "እኔ በዳኝነቴ የሁለታችሁንም ነገር ያለአድሎ በማመዛዘን እመለከታለሁ፤ እንጂ ወዳጄ ነህ ብዬ ላንተ የምሰራልህ ነገር የለም።" ብሎ መለሰለት።

ወዳጁ ተቆጥቶ "ያንተ ስራ ዳኝነት ነው። በዳኝነት ስራህ እኔን ወዳጅህን ልትረዳኝና ልትጠቅመኝ ይገባል። ይህን ካልፈቀድክ ያንተ ፍቅር ለኔ ምን ይጠቅመኛል?" አለው። ዳኛውም መልሶ "አንተ በእውነት ወዳጄ ከሆንክ ፍርድ ማጉደልን የሚያህል ትልቅ ሀጢያት እንዳልሰራ ታበረታታኛለህ? ህሊናዬንና ክብሬን የሚያዋርድ ተግባር እንድሰራ ትጠይቀኛለህ? ወዳጅነትህ ለዚህ ከሆነ ወዳጅነትህና ፍቅርህ አይጠቅሙኝም።" በማለት መለሰለት።

*(ከበደ ሚካኤል፣ ታሪክና ምሳሌ ከተሰኘው መጽሐፍ ለማስተማሪያነት እንዲመች ተሻሽሎ የተወሰደ)*

## ተግባር ፩

## መምህር፡-

- ❖ ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች መሰረት ያሰፈሯቸውን ግምቶች ካዳመጡት ምንባብ ጋር መዛመዱን እንዲገመግሙ እድል ይስጧቸው።

  - ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንዳቸውን ግምት ሌሎቹ እንዲገመግሙ ያድርጉ።
  - የሰጡት ግምት ከተደመጠው ሀሳብ ጋር ለተዛመደላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው።

- ምስሉ ከተደመጠው ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡
- የተማሪዎችን ምላሽ በመመልከት በምስሉ ላይ ካሉ ሰዎች አቀማመጥና ከሚዛኖቹ ጋር አዛምደው ምስሉ ከተደመጠው ጽሑፍ ጋር ያለውን ትስስር ያብራሩላቸው፡፡

❖ በተማሪ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

❖ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡

❖ የማዳመጥ ችሎታችን የተሻለ ለማሳደግ የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን ወይም ታሪኮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን ይደግፉ፡፡

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

❖ ተማሪዎች የመዘገቧቸው እንግዳ ቃላት ካሉ ለቃላቱ እርስ በእርስ ፍቺ እንዲሰጣጡ ያድርጉ፡፡

❖ ከምንባቡ ባዳመጧቸው አዳዲስ ቃላት አምስት ተራ ዓረፍ ነገር እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡

❖ ተግባሩን ከመስራታቸው በፊት ሳይቸገሩ ይሰሩ ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡

- ❖ ተግባሩን በሚሰሩበት ጊዜ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እየተዘዋወሩ በመመልከት ያግዟቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም የመሰረቷቸውን ዓረፍተ ነገሮች ትክክለኛነት (ከቋንቋ፣ ከሥርዓተ ነጥብና ከይዘት ትክክለኛነት) አንጻር በመፈተሽ እርማት ይስጧቸው፡፡

**ቃላት**

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያሉትን የማዛመድ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተያዩና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡

### የተግባር ፩ መልስ

1. ለ
2. መ
3. ሀ
4. ሐ
5. ሠ

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ የተዘረዘሩ ቃላት ከመጨረሻ ቅጥያቸው አንጻር በመደብ በመደብ እንዲመድቡ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ለማቅለል ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በታዘዙት መልኩ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተግባሩን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው እንደጨረሱም የሰሩትን ሥራ ይዩላቸው፡፡ በሚከተለው መልኩ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

| በ"ች" የሚጨርሱ | በ"ዎች" የሚጨርሱ | በ"ነት" የሚጨርሱ |
|---|---|---|
| በላች | ጫማዎች | የዋህነት |
| አየች | ገበሬዎች | ደግነት |
| ሰራች | ተማሪዎች | ቸርነት |

## መነጠልና ማጣመር

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ላይ “መልካም” ከሚለው ቃል ላይ ሌላ ቃላትን በመጨመር ጥምር ቃል እንዲመሰርቱ የሚያዘውን ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ እንዲሰሩት በቂ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሰሩትን ተግባር በማየት ለተሳሳቱት እርማት፤ በትክክል ለሰሩት የማበረታቻ ቃላትን ተጠቅመው ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን ለማበልጸግ በመርጃ መሳሪያነት ስዕል፣ የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ጥቁር ሰሌዳ … እንዳስፈላጊነቱና እንደመማሪያ ክፍሉ አመችነት በመምረጥ ይጠቀሙ፡፡
- ✓ ተግባሩን በትክክል መሥራታቸውን ለመመዘን ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## 🕮 ንባብ

### “ሀሁ…”

**መምህር፡-**

**ተግባር ፩**

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን “ሀሁ…” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች”ሀሁ…”የሚለውን ምንባብ በግል አንብበው ሲጨርሱ በጥንድ እየተነሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

## አንብቦ መረዳት

- ❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባር ፩ መልስ**

1. ለ
2. ሐ
3. ሀ

**ተግባር ፪**

- ተማሪዎች ሶስት ወይም አራት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አወያያ (መሪ) እዲመርጡ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አባላቱ የምንባቡ መልዕክት በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሁለት ዓረፍተ ነገር ጠቅለል አድርገው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች በታዘዙት መልኩ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡
- ከዚያም ከቡድን አባላቱ መካከል አንድ ተማሪ እርስዎ መርጠው በጽሁፍ ያዘጋጁትን የቡድኑን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ከገለጹ በኋላ እርስዎ ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር ፩ ላይ የቀረቡት ቃላት “ሀሁ…” ከሚለው ምንባብ የወጡት ስለሆኑ በምንባብ ውስጥ ባላቸው አውድ ተማሪዎች እንዲፈቷቸው ምሳሌ በመስጠት አሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡ መሰረት አድርገው ቃላቱን እየፈቱ መሆናቸውን ይከታተሉ፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

### የተግባር ፩ መልስ

1. ማወቅ
2. ዘበኛ
3. ጎዳና
4. ትምህርት
5. ተግሳፅ

## ተግባር ፪

## ምልክቶች ከመጠሪያዎቻቸው ጋር ማስተሳሰር

**መምህር፡-**

- የጥያቄ ምልክትን ለተማሪዎችን ይከልሱላቸው፡፡
- በሂሳብ ትምህርታቸው ላይ የሚገለገሉባቸው ምልክቶችን ተማሪዎቹ እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡ ሀሳቡ የበለጠ የተብራራ ይሆን ዘንድ የተለያዩ ምልክቶችን የሚያሳዩ ካርዶች፣ ስዕሎች፣ ባለቀለም ወረቀቶችና ሌሎችንም በመጠቀም ምልክቶቹን ከፅንሰ ሀሳቦቻቸው ጋር በማያዝ ይግለፁላቸው፡፡
- ከዚያም በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት በተግባር ሁለት የቀረቡትን ምልክቶች ከስያሜዎቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባር ፪ መልስ**

1. ለ
2. ሀ
3. ሐ
4. መ
5. ሠ

- በተጨማሪ ተማሪዎች ምልክቶችን ከተለያዩ ሀሳቦች ጋር በማጣበር ማንበብና መረዳት እንዲችሉ በትዕዛዝ ፫ ላይ ያለውን ተግባር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ይዘቱን የበለጠ እንዲረዱት ለማድረግ ሌሎች ምልክቶችን ከተለያዩ ሀሳቦች ጋር በማጣመር እንዲያነቡ የሚያደርጋቸው ተግባር በመቅረፅ ተማሪዎች እንዲሞክሩት ያድርጉ፡፡

### የተግባር ፫ መልስ

1.X 2.÷ 3.+ 4.- 5.=

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- ተማሪዎች "ሀሁ…" በሚለውን ምንባብ በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው በማንበብ እንደአባትና ልጅ በመሆን በቃላችሁ እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡
- እንደአባትና ልጅ በመሆን በቃላችሁ ተለማምደው የመጡ ተማሪዎችን ጥንድ ጥንድ ሆነው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ እድል ሰጧቸው፡፡

- እገዛና ማበረታቻም ይስጧቸው፡፡
- በቃላቸው ሲያቀርቡ ምንባቡን በምን መልኩ እንዳቀረቡት በመከታተያ ቅጽ በመመዝገብ ተከታተሉ፡፡
- ተግባሩን በመከታተያና በመገምገሚያው ቅጽ መሰረት ግብረ-መልስ ይስጡ፡፡

| | መስፈርቶች | በጣም ጥሩ | ጥሩ | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|
| | | ✓ | ✓ | ✓ |
| ሀ | የተፃፉትን ቃላት በትክክል በቃል የመያዝ ብቃት | | | |
| ለ | የተዘለሉ የቃላት ብዛት | | | |
| ሐ | በትክክለኛ ድምጸት ያልቀረቡ ሥርዓተ ነጥቦች ብዛት | | | |
| መ | በምልልሱ ያለ የመደማመጥ ሁኔታ | | | |

- ከላይ ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀውን የትግበራ መከታተያና መገምገሚያ ቅጽ እንዳስፈላጊነቱ ይጠቀሙበት።
- ተማሪዎችም እርስበርስ የብጤ እርማት ይሰጣጡበት ዘንድ በቻርት አዘጋጅተው ለተማሪዎች የሚታይ ቦታ ላይ ያድርጉላቸው።

## ጽሕፈት

### ተግባር ፩

**መምህር፦**

- ስለተቃራኒ ፍቺ ማብራሪያና ምሳሌ ከሰጡ በኋላ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያለውን ተግባር የክፍል ሥራ ይስጧቸው።
- የሰሩትን የክፍል ስራ እዩላቸው።
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው።

**የተግባሩ ፩ መልስ**

10. ክፉ 4. እውነት

11. ጎበዝ 5. እርግማን

12.መጥፎ

**ተግባር ፪**

- ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት **መልካም ምግባር** እና **መጥፎ ምግባር** የሚባሉ ነገሮች ከተማሪዎች ጋር ውይይት ያድርጉ፡፡ ከዚያም በትዕዛዝ ፪ ላይ ያለውን ተግባር እንዴት መስራት እንዳለባቸው ያስረዷቸው፡፡
- ተግባር ያሰሯቸው፡፡ በመቀጠል ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው፡፡

**ተግባር ፫**

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፫ ላይ በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገር መስራት ይችሉ ዘንድ ምሳሌውን ያብራሩላቸው፡፡ ከዚያም ተግባሩን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶች ላይ በተፃፉ ቃላት፣ ባለቀለም ወረቀቶች ላይ ያሉ ቅርፆችን፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣ … ተጠቅመው ተማሪዎቹ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲሰሩ በማድረግ ያግዟቸው፡፡›

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “ትክክለኛ ዳኛ” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ “ሀሁ…” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤የአንብቦ መረዳት፤የቃላት፤የማጣመርና የመነጠል፤ የፅህፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኂላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

## ምዕራፍ ስምንት
## የምግብ አዘገጃጀት

18

ክፍለ ጊዜ

### የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ፅሑፍ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ያደራጃሉ
- ካዳመጡት ምንባብ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ
- ከምንባቡ ውስጥ ተራ ዓረፍተ ነገሮችን ይለያሉ
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ
- አጫጭር ታሪኮችን አቀላጥፈው ያነባሉ

### የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ድምፅን የመገንዘብ ችሎታ
- ንባብ
- ፅህፈት
- ማፍለቅና መረዳት
- ድምፀት

## ((( ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች በመገመቻ ቻርት ላይ እንዲያሰፍሩ ይዘዟቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡ በተጨማሪም ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላት ሲገጥሟቸው እንዲመዘግቡ ያድርጓቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

## ተጋቢኖ

ወ/ሮ መናሹ ለቅሶ ገጠማቸው፡፡ በጠዋት ተነስተውም ወደ ለቅሶው ሄደዋል፡፡ ብሩክም ባለው ወጥ ቁርሱን በልቶ ወደ ትምህርት ቤት ሔደ፡፡ ከትምህርት ቤት ሲመለስ እናቱ አልመጡም፡፡ ወጥም የለም፡፡ ብሩክም ራበው፡፡ "እንዴ እናቴ ሽሮ ስትሰራ አይቼ አውቅ የለ ለምን አልሰራም" ብሎ አሰበ፡፡

ሐሳቡንም እንደሚከተለው ተገበረው፡፡ በመጀመሪያ ቀይ እና ነጭ ሽንኩርት ልጦ ከተፈ፡፡ ቲማቲሙንም ቀጠቀጠ፡፡ ድስቱን እሳት ላይ ጥዶ ቀይ ሽንኩርቱንና ዘይቱን ጨምሮ አበሰለ፡፡ የተቀጠቀጠውን ቲማቲም በመጨመር ትንሽ ካበሰለ በኋላ መጠነኛ ውሃ ከለሰ፡፡ ውሃው ሲፈላ ምጥን ሽሮ ጨምሮ በሚገባ አዋሃደው፡፡ነጭ ሽንኩርቱንም ጨምሮ በደንብ አንተከተከው፡፡ ከማውጣቱ በፊት መብሰሉን አረጋገጠና ጨው ጨምሮ አወጣው፡፡

ከዚያም እንጀራ ላይ አድርጎ ሊበላ ሲል እናቱ በጣም ደክሟቸው መጡ፡፡ እግራቸውን አጥቦ ምሳ አቀረበና አብረው በሉ፡፡ ወ/ሮ መናሹም በጣም ስለተደሰቱ ብሩክን መረቁት፡፡

## ተግባር ፩

### መምህር፡-

❖ ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች መሰረት ያሰፈሯቸውን ግምቶች ካዳመጡት ምንባብ ጋር መዛመዱን እንዲገመግሙ እድል ይስጧቸው፡፡

- ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንዳቸውን ግምት ሌሎቹ እንዲገመግሙ ያድርጉ፡፡
- የሰጡት ግምት ከተደመጠው ሀሳብ ጋር ለተዛመደላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ምስሉ ከተደመጠው ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡

- የተማሪዎችን ምላሽ በመመልከት በምስሉ ላይ ካሉ ሰዎች አቀማመጥና ከሚዛኖቹ ጋር አዛምደው ምስሉ ከተደመጠው ጽሑፍ ጋር ያለውን ትስስር ያብራሩላቸው፡፡

➢ በተማሪ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

➢ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡

➢ የማዳመጥ ችሎታችን የተሻለ ለማሳደግ የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን ወይም ታሪኮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን ይደግፉ፡፡

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

❖ ተማሪዎች የምንባቡን ታሪክ በቅደም ተከተል በማደራጀት በዓረፍተ ነገር እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡

❖ ተግባሩን ከመስራታቸው በፊት ሳይቸገሩ ይሰሩ ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡

❖ ተግባሩን በሚሰሩበት ጊዜ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እየተዘዋወሩ በመመልከት ያግዟቸው፡፡

❖ በመጨረሻም የመሰረቷቸውን ዓረፍተ ነገሮች ትክክለኛነት (ከቋንቋ፣ ከሥርዓተ ነጥብና ከይዘት ትክክለኛነት) እንዲሁም የታሪኩን ፍሰት መጠበቃቸውን በመፈተሽ እርማት ይስጧቸው፡፡

| | |
|---|---|
| **መጀመሪያ** | **ብሩክ እናቱ ለቅሶ ስለሄዱ ወጥ አልቆበት ራበው፡፡** |
| **ከዚያ** | ብሩክ ጣፋጭ ሽሮ ወጥ ሰራ፡፡ |
| **በመቀጠል** | ብሩክ ምሳውን አቅርቦ ሊበላ ሲል እናቱ መጡ፡፡ |
| **በመጨረሻ** | ብሩክ ምሳውን ከእናቱ ጋር በላ፡፡ |

## ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ላሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተያዩና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባር ፩ መልስ**

1. ንጋት
2. ተመገበ
3. ተመልክቼ
4. ትንሽ
5. ውሃ ጨመረ

(ሌሎች ተዛማጅ ፍቺዎችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡)

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ የተዘረዘሩ ቃላት የመነሻ ሆሄያትን እንዲለዩ ድርጉ፡፡
- ✓ ተግባሩን ለማቅለል ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በታዘዙት መልኩ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተግባሩን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው እንደጨረሱም የሰሩትን ሥራ ይዩላቸው፡፡ በሚከተለው መልኩ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

**መልስ፡-**

1. እንደ-ፃፈ
2. የ-ተቆጣ
3. ከ-መጣ
4. ስለ-መጣ
5. ለ-እናት

## ተግባር ፫

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፫ የተቀመጡትን ምስሎች ከትክክለኛ መጠሪያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የምስሎቹን ሁኔታ በድምፅ ይንገሯቸውና ስማቸውን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡

## ንባብ

## የተመጣጠነ ምግብ

**መምህር፡-**

**ተግባር ፩**

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን **የተመጣጠነ ምግብ** የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች **የተመጣጠነ ምግብ** የሚለውን ምንባብ በግል አንብበው ሲጨርሱ ከምንባቡ የተረዱትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## አንብቦ መረዳት

- ❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባር ፩ መልስ**

4. እውነት
5. ሐሰት
6. እውነት

# 🗝 ቃላት

**ተግባር ፩**

- ተማሪዎች በመማሪያ መፅሃፋቸው ላይ ያሉትን ቃላት በመደብ በመደብ እንዲያስቀምጡ ይደግፏቸው፡፡
- ምሳሌ በመስጠት ተግባሩን ተረድተው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- በሚከተለው መልኩ እርማት ይስጧቸው፡፡

| ድርጊት የሚያሳዩ | ለምግብ መጠሪያ የሚሆኑ | መጠንን የሚገልፁ |
|---|---|---|
| 1. ሰራች | 1. ተጋቢኖ | 1. ረጅም |
| 2. ጠጣ | 2. ዳቦ | 2. ቀጭን |
| 3. ጎረሰች | 3. እንጀራ | 3. አጭር |
| 4. በላ | 4. ወጥ | 4. ወፍራም |

**ተግባር ፩**

**መምህር፡-**

- ➢ በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር ፪ ላይ የቀረቡት ቃላት **የምግብ አዘገጃጀት** ጋር በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው ቃላት ናቸው፤ቃላቱን ከተስማሚ ቃላት ጋር እንዲያጣምሩ ያድርጉ፡፡
- ➢ ሌሎች ተጨማሪ ተግባርም ይስጧቸው፡፡
- ➢ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፪ መልስ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ሀ | 3. ለ | 5. ሀ |
| 2. ለ | 4. ለ | 6. ሀ |

### ተግባር ፫

**መምህር፡-**

- በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር ፫ ላይ የቀረቡትን ድርጊት አምልካች ምስሎችን ከቃላቱ ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡
- ሌሎች ድርጊት አመልካች ምስሎችን በማሳዬት እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

# ፅህፈት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- የተመጣጠነ ምግብ ከሚለው ምንባብ ውስጥ ቢያንስ ሶስት ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ይገዟቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተግባሩን እንደሚመቻቸው አድርገው እንዲሰሩት ይደግፏቸው፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ ልዩ ልዩ ቃላት ቀርበዋል፤ቃላቱን መሰረት በማድረግ ተማሪዎቹ አረፍተ ነገሮችን እንዲሰሩ ያድረጉ፡፡
- ተማሪዎች የሰሯቸውን ዓረፍተ ነገሮች እርስበርስ እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ ያግዟቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተግባሩን እንደሚመቻቸው አድርገው እንዲሰሩት ይደግፏቸው፡፡
- ሌሎች ቃላትን በመስጠት ዓረፍተ ነገሮችን እየመሰረቱ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡
- እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

**መምህር፦**

- **የሚከተለውን አጭር የበዓል ታሪክ በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ለተማሪዎቹ ያንብቡላቸው፤**
- **በመቀጠል በተማሪዎች መፅሃፍ ትዕዛዝ ፫ ላይ በተቀመጠው አካሔድ መሰረት ራሳቸው ታሪክ እንዲፅፉ ይደግፏቸው።**
- **ተማሪዎች ሲፅፉ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው፤ ማስተካከያ ስጧቸው።**

### አረፋ

ልክ የዛሬ ሁለት ዓመት በአረፋ በዓል እለት ጓደኛዬ ሁሴን ቤት ነበርኩ፤ የተለያዩ ምግቦች ተሰርተው በሚያምር ሁኔታ ተደርድረዋል። ሁሴንና ቤተሰቡ መስጊድ ደርሰው እስኪመጡ ድረስ እቤት እንድሆን ነግረውኝ ሔዱ። ሰግደውም ተመለሱ።በቴምር አፍጥረው የተደረደረውን ምግብ መመገብ ጀመርን። ከዚያም በግ በማረድ ሶስት ቦታ ተመደበ፤ አንደኛውን ለራሳቸው፤አንዱን ለምስኪኖች፤ሌላኛውን ደግሞ ለቤተሰብ ግብዣ በማድረግ ከፋፈሉት።የራሳቸውን በጋራ ጠባብሰው ከበሉ በኋላ ለምስኪኖች ሊሰጡ ሔዱ።ለእኔም ያዘጋጁልኝን ምግብ እየተመገብኩ ህብረትና ፍቅራቸውን ከልቤ አደነኩ።በመጨረሻ ለቤተሰብ ግብዣ ያዘጋጁትን ምግብ ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ጠርተው፤ ቡና በማፍላት በጋራ በዓሉን አከበሩ። ይህ ተግባራቸው እጅግ ደስ የሚልና አስተማሪ በመሆኑ ሁሌም በየአመቱ አረፋ ሲመጣ ጓደኛዬ ሁሴንን አስታውሰዋለው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "ተጋቢኖ" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ "የምግብ አዘገጃጀት" የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤የአንብቦ መረዳት፤ የቃላት፤ የፅህፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው።

## የማጠቃለያ ተግባራት

**ተግባር ፩**

**መምህር፡-**

- ተማሪዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለቀረቡላቸው ቃላት ትክክለኛ ተጣማሪ የሚሆኑ ቃላትን በመፈለግ እንዲያጣምሩ ያድርጉ፡፡
- በሚከተለው መልኩ እርማት ይስጧቸው፡፡

**መልስ፡-**

1. **ፀጉር** ሰሪ
2. **ዶሮ** አርቢ
3. **መዝሙር** ዘማሪ
4. **ቀለም** ቀቢ
5. **ዜና** አንባቢ

## ተግባር ፪

መምህር፦-

- በሰንጠረዡ ውስጥ የተለያዩ ፊደላት ቀርበዋል፤ ፊደሎችን ወደላይ፣ ወደታች፣ ወደጎን እንዲሁም አግድም በማገናኘት ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- በሚከተለው መልኩ እርማት ይስጧቸው፡፡

| መ | ጋ | ዝ | ቅ | ቤ |
|---|---|---|---|---|
| ጥ | ዘ | ን | ባ | ባ |
| ረ | ሃ | ብ | ት | ህ |
| ጊ | ታ | ር | ጉ | ል |
| ያ | ቤ | ተ | ሰ | ብ |

**ሊመሰረቱ የሚችሉ ቃላት በከፊል**

1. መጥረጊያ
2. መጋዝ
3. ዝንብ
4. ቅባት
5. ቅቤ
6. ባህል
7. ዘንባባ
8. ጊታር
9. ብር
10. ረሃብ
11. ቤተሰብ
12. ልብ
13. ትጉ
14. ሃብት
15. ጋዝ

(ሌሎች ቃላትም ሊመሰረቱ ይችላሉ)

| አማርኛ<br>፪ኛ ክፍል | ምዕራፍ ዘጠኝ<br>ዲጅታል ቁስ | 18<br>ክፍለ ጊዜ |
| --- | --- | --- |

## ➢ የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ካዳመጡት የምንባብ ጽሑፍ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ያደራጃሉ፡፡
- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር ያነባሉ፡፡
- ዓረፍተ ነገር በትክክል ይጽፋሉ፡፡

## ➢ የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ድምፅን የመገንዘብ ችሎታ
- ንባብ
- ፅህፈት
- ማፍለቅና መረዳት

## ((( ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ። ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው።
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው።
- ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች በመገመቻ ቻርት ላይ እንዲያሰፍሩ ይዘዟቸው።
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው።
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው።
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው።
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው። ምላሻቸውን ይቀበሏቸው።

## መረጃ ማግኛ ቁሶች

መረጃ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው። በመረጃ አማካኝነት ዓለምን ማስተሳሰርና ህይወትን ቀላል ማድረግ ይቻላል። የሰው ልጆች መረጃን በተለያዩ መንገዶች ያገኛል። ይኸውም በድምጽ፣ በጽሑፍ፣ በድምጽና በምስል (በቪዲዮ) … ያገኛሉ። በድምጽ የምናገኘው መረጃ በስልክ፣ በሬዲዮና በመሳሰሉት ሊቀርብ ይችላል። በጽሑፍ ደግሞ በጋዜጣ፣ በደብዳቤ … ሊቀርብ ሲችል በድምጽና በምስል ደግሞ በቴሌቪዥን፣ በላፕቶፕ በስልክና በመሳሰሉት እናገኛለን። መረጃ የምናገኝባቸው ቁሶች በድሮና በአሁኑ ዘመን የተለያዩ ናቸው።

## …ተማሪዎች በድሮ ዘመን መረጃ እናገኝባቸው የነበሩ ቁሶች አነማን ናቸው? በአሁን ዘመንስ?…

በድሮ ዘመን የመረጃ ልውውጥ የሚካሄደው በጋዜጣ፣ በደብዳቤና በመሳሰሉት ነበር፡፡ በተጠቀሱት ቁሶች መረጃ ለማግኘት በተፈለገው ጊዜ ፈጥኖ ላይገኝ ይችላል፡፡ ሁሉም ቦታዎች ለማዳረስም ያዳግታል፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ይህ ችግር ተፈቷል፡፡ በኢሜል፣ በቴሌ ግራም፣ በፌስ ቡክ፣ በቲዩተር ወዘተ አማካኝነት ዓለም ላይ እየሆነ ያለውን ነገር በሴኮንዶች እናገኛለን፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ለማናገኝት የምንጠቀምባቸው ዲጂታል ቁሶች እንደ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ስልክ፣ ታብሌት፣ ላፕቶፕ፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሶች ህይወትን በማቅለሉ ረገድ ትልቅ ድርሻ ቢኖራቸውም በአግባቡ ካልተጠቀምንባቸው ጉዳታቸው ብዙ ነው፡፡

### ተግባር ፩

### መምህር፡-

- ❖ ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች መሰረት ያስፈሯቸውን ግምቶች ካዳመጡት ምንባብ ጋር መዛመዱን እንዲገመግሙ እድል ይስጧቸው፡፡
    - ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንዳቸውን ግምት ሌሎቹ እንዲገመግሙ ያድርጉ፡፡
    - የሰጡት ግምት ከተደመጠው ሀሳብ ጋር ለተዛመደላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡

- ምስሉ ከተደመጠው ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡

❖ በተማሪ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

❖ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡

❖ የማዳመጥ ችሎታቸውን የተሻለ ለማሳደግ የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን ወይም ታሪኮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን ይደግፉ፡፡

**ተግባር ፪**

**መምህር፡-**

❖ የመረጃ ማግኛ ቁሶችን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ ቡድን መስርተው እንዲወያዩ ያመቻቹላቸው፡፡

- ከአራት እስከ ስድስት አባላት ያለው ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- የቡድኑ መሪና ጸሐፊ እንዲመርጡ ያግዟቸው፡፡
- የቡድን መሪውንና ጸሐፊውን ድርሻ ይንገሯቸው፡፡ (የቡድኑ መሪ የአወያይነት ሚና እንዲጫወትና በመጨረሻም የሚያቀርብ እንደሆነ፤ ጸሐፊው ደግሞ በውይይቱ የተነሱ ሀሳቦችን በአጭር በአጭር እንዲይዝ ይንገሯቸው፡፡)

- የሚወያዩበት ርዕሰ ጉዳይ ግልጽ እንዲሆንላቸው መነሻ ሀሳብና ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም በየቡድናቸው እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- የውይይቱን ሂደት እየተዘዋወሩ በመቃኘት የቡድኖችን እንቅስቃሴ ይገምግሙ፡፡
- ደከም ያለ ተሳትፎ ያለው ቡድን ካለ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ከዚያም በቡድን መሪያቸው አማካኝነት ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያመቻቹላቸው፡፡

❖ የየቡድኖቹ ሀሳብ ከቀረበ በኋላ ከሰጡት ሀሳብ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

❖ ተግባሩን ሲያሰሩ የአካቶ ትምህርትን የተማሪዎቹን ሁኔታ ባማከለ መልኩ ይተግብሩ፡፡

❖ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ለማካተትና ፈጣኖችንም ለማገዝ ተጨማሪ ተግባር ይስጧቸው፡፡ ተግባሩ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን በማዳመጥ ያዳመጡትን ሀሳብ እንዲናገሩ ማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ (እንደተማሪዎቹና መማሪያ ክፍሎች ሁኔታ ቤታቸው እንዲሰሩ የሚሰጧቸውን ተግባር እንዳመችነቱ ያዘጋጁ፡፡)

## 🔑 ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ❖ ተማሪዎች ከማዳመጥ ምንባቡ የወጡ ቃላትን ጥንድ ጥንድ በመሆን ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ❖ የቃላቱን ዐውድ በደንብ እንዲረዱት እንዳስፈላጊነቱ ቃላቱ ያሉበትን ዓረፍተ ነገሮች ለተማሪዎች ቢያነቡላቸው ጥሩ ነው፡፡
- ❖ ተግባሩን ከመስራታቸው በፊት ሳይቸገሩ ይሰሩ ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም የሰጡትን ምላሽ ትክክለኛነት በመመልከት እርማት ይስጧቸው፡፡
- ❖ ሌሎች ተጨማሪ ቃላትንም በመስጠት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡

### ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ➢ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፪ ላይ በምስል የቀረቡትን ዲጂታል ቁሶች ከስያሜዎቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ይዘዟቸው፡፡

- ➢ ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- ➢ በተጨማሪም ተግባሩን የበለጠ እንዲያዳብሩት ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣... ይጠቀሙ፡፡

## 🕮 ንባብ

# የጊዜ ብክነት

**መምህር፡-**

**ተግባር ፩**

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለውን "የጊዜ ብክነት" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

**ተግባር ፪**

- ተማሪዎች ሶስት ወይም አራት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አወያያ (መሪ) እዲመርጡ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አባላቱ የምንባቡ መልዕክት በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሶስት ዓረፍተ ነገሮች ጠቅለል አድርገው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች በታዘዙት መልኩ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡
- ከዚያም ከቡድን አባላቱ መካከል አንድ ተማሪ በጽሁፍ ያዘጋጁትን የቡድኑን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ከገለጹ በኋላ እርስዎ ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያለውን የማዛመድ ተግባር የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡

- የማዛመድ ተግባሩ ከሰሩ በኋላ የብጤ እርማት እንዲያካሂዱ ያመቻቹላቸው፡፡
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባሩ ፩ መልስ**

| | |
|---|---|
| 13. ሐ | 4. ሠ |
| 14. ሀ | 5. መ |
| 15. ለ | |

### ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ተግባር ፩ ላይ የቀረቡት ቃላት "የጊዜ ብክነት" ከሚለው ምንባብ የወጡ ስለሆኑ በምንባብ ውስጥ ባላቸው ዐውድ ተማሪዎች እንዲፈቷቸው ምሳሌ በመስጠት ያሳዩዋቸው፡፡

- ተማሪዎች ምንባቡ መሰረት አድርገው ቃላቱን እየፈቱ መሆናቸውን ይከታተሉ፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## መነጠልና ማጣመር

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ በቃል መጀመሪያ ላይ ሊመጡ ስለሚችሉ ቅጥያዎች በልጆቹ ደረጃ መጥነው ያስረዷቸው፡፡ የማብራሪያ ዓላማ ስለቅጥያዎቹ አይነትና አገልግሎት ማሳወቅ ሳይሆን መነጠል እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡
- ✓ ማብራሪያው ለተማሪዎቹ ግልጽ ይሆን ዘንድ በተለያዩ አስረጅዎች ይደገፍ፡፡
- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ላይ "ስነ-፣ ልበ- እና ቤተ-" በሚሉ ቅድመ ቅጥያዎች ከተዘረዘሩ ቃላት ጋር ተስማሚያቸውን በመምረጥ አጣምረው እንዲጽፉና እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ ይሰሩት ዘንድ ስለ አሰራሩ ማብራሪያ እና በቂ ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ እንዲሰሩት በቂ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሰሩትን ተግባር በማየት ለተሳሳቱት እርማት፤ በትክክል ለሰሩት የማበረታቻ ቃላትን ተጠቅመው ያበረታቷቸው፡፡

- ✓ ትምህርቱን ለማበልጸግ በመርጃ መሳሪያነት ስዕል፣ የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ጥቁር ሰሌዳ ... እንዳስፈላጊነቱና እንደመማሪያ ክፍሉ አመችነት በመምረጥ ይጠቀሙ፡፡
- ✓ ተግባሩን በትክክል መሥራታቸውን ለመመዘን ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፪

### መምህር፡-

- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለማጣመር ተግባር የቀረቡ ቃላትን አጣምረው እንዲጽፉና እዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ አጣምረው የጻፏቸውን ለማንበብ ሁለት ሁለት ተማሪዎችን በየተራ እያስነሱ አንደኛው ተማሪ ከመማሪያ መጽሐፉ ተነጣጥለው የተጻፉትን ሲያነብ ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ተጣምረው የተጻፉ ቃላትን እንዲያነብ ያድርጉ፡፡
- ✓ ነጣጥለውና አጣምረው ሲያነቡ የሚኖሩ ስህተቶችን በመመልከት ቃላዊ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ ላልተገበሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ተግባር ይስጧቸው፡፡ ለፈጣን ተማሪዎች ደግሞ የመጀመሪያና የመጨረሻ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት በመስጠት እንዲነጣጥሉና እንዲያጣምሩ ያግዟቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- ተማሪዎች "የጊዜ ብክነት"የሚለውን ምንባብ በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳየት የተመረጠውን ምንባብ አንድ ጊዜ በጥሩ የአነባበብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡
- ከዚያም በአንቀጽ እየተከፋፈሉ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- የመከታተያ ቅጽ በሰሌሌዳ ላይ ወይም በቻርት አዘጋጅተው በሚታይ ቦታ ያድርጉላቸው፡፡
- የመከታተያ ቅጹን መሰረት አድርገው እርስ በርስ ደቂቃ በመያዝ የንባብ ፍጥነትንና በአቀላጥፎ ማንበብ ወቅት የሚጠበቁ ብቃቶችን እንዲተገብሩ ያድርጓቸው፡፡
- ተግባሩን በመከታተያና በመገምገሚያው ቅጽ መሰረት በመከታተል ግብረመልስ ይስጡ፡፡

### ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በአቀላጥፎ ማንበብ ስር በትዕዛዝ ፪ ያለውን ተግባር ለተማሪዎቹ ያሰሯቸው፡፡
    - አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክትና ቃለ አጋኖ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ምን አይነት ድምጸት ሊኖራቸው እንደሚችል ለተማሪዎችን ይከልሱላቸው፡፡
    - ሀሳቡ የበለጠ የተብራራ ይሆን ዘንድ የተለያዩ አስረጂዎችን በመጠቀም ያስረዷቸው፡፡

- ከዚያም በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት በተግባር ሁለት የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያድርጉቸው፡፡

✓ ዓረፍተ ነገሮቹን የተለያዩ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

✓ እጅ የማያወጡ (ለማንበብ ፍቃደኛ ያልሆኑ) ተማሪዎች ካሉም እነሱም እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

✓ የአነባበባቸውን ትክክለኛነት አስመልክቶ እርማት ይስጧቸው፡፡

✓ የተማሪዎችን የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡

## ጽሕፈት

### የቃል ጽሕፈት

**መምህር፡-**

✓ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች እያነበቡላቸው በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

1. ዓለም አንድ መንደር ሆናለች፡፡
2. ዲጂታል ቁሶች ህይወትን ያቀላሉ፡፡
3. ህጻናት ለመምህራቸውና ለወላጆቻቸው መታዘዝ አለባቸው፡፡

✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በወረቀት ፅፈው ይስጧቸው፡፡

✓ በትክክል መጻፋቸውን እየዞሩ ይከታተሏቸው፤ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

### የመጽሔት ምላሽ

**መምህር፡-**

➢ በየዕለቱ በክፍል ውስጥ ከሚያከናውኑት ተግባር ሁለቱን እንዲመዘግቡ ያድርጉ፡፡

➢ ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ ከተማሩት ትምህርት ውስጥ ሁለቱን ተግባር በአራት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

- ዓረፍተ ነገሮችን ሲጽፉ ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- የጻፏቸውን ዓረፍተ ነገሮች ከሥርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም፣ ከዓረፍተ ነገር አወቃቀር እና ከፊደል አጻጻፍ ትክክለኛነት አንጻር በመገምገም እርማት ይስጧቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "መረጃ ማግኛ ምንባብ" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ "የጊዜ ብክነት" የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ የአንብቦ መረዳት፤ የቃላት፤ የማጣመርና የመነጠል፤ የጽሕፈት...ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

## ምዕራፍ አስር

## የዱር እንስሳት

18

ክፍለ ጊዜ

### ➢ የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ዋናውን መልዕክት በፅሑፍ ዘገባ ያቀርባሉ
- የምንባቡን ሐሳብ ከተጨባጭ ህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ
- ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ
- አቀላጥፈው ያነባሉ
- ለደረጃው የሚመጥን ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ

### ➢ የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ድምፅን የመገንዘብ ችሎታ
- ንባብ
- ፅህፈት
- ማፍለቅና መረዳት
- ድምፀት

## ((( ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች በመገመቻ ቻርት ላይ እንዲያሰፍሩ ይዘዟቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡ በተጨማሪም ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላት ሲገጥሟቸው እንዲመዘግቡ ያድርጓቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

# ብልኋ ዝንጀሮ

ዘምዘምና ናትናኤል ቅጠል ለመልቀም ወደ ጫካ ሔዱ፡፡ቅጠል እየለቀሙ እያለ አንዲት ትንሽ ዝንጀሮ ወድቃ አዩ፡፡ ሲያነሷትም እግሯ መሰበሩን ተረዱ፡፡በጣም ስላሳዘነቻቸው ወደ ቤት ይዘዋት ሔዱ፡፡

እግሯንም በሸንበቆና በጨርቅ አሰሩት፡፡የትንሿ ዝንጀሮ እናት ለልጇ ምግብ ይዛ መጣች፡፡ልጇ ግን በቦታው የለችም፡፡ፍለጋ ስትወጣ የእነዘምዘምን ኮቴ ሰሙ፡፡ እነሱ እንደወሰዱባት ገመተች፡፡

በጣም ስለተናደደች ወደመንደሩ ገብታ አንድ ህፃን ልጅ ይዛ መሮጥ ጀመረች፡ ፡የሰፈሩ ሰዎች ህፃኑን ይዛ ስትሔድ ስላዩዋት ተከተሉዋት፡፡ሊደርሱባት ግን አልቻሉም፡፡ልጁን ይዛ ትልቅ ዛፍ ላይ ወጥታ ቁጭ አለች፡፡ሰዎቹም ዛፍ ላይ ለመውጣት ቢሞክሩም አቃታቸው፡፡እሷም ዛፍ ላይ ቁጭ ብላ አልወርድም አለች፡፡

ዘምዘምና ናትናኤል ወደቤት ሔደው ለትንሿ ዝንጀሮ ወተት ሰጧት፡፡ከዚያም ዞር ዞር ብለው ወላጆቻቸውን ቢፈልጓቸው አጧቸ፡፡ በመደናገጥ ወደ ጎረቤት ሔዱ ግን በአካባቢው ማንም ሰው የለም፡፡ግራ ገብቷቸው ዝንጀሮዋን ቤት ውስጥ አስቀምጠው መነጋገር ጀመሩ፡፡ናትናኤል "ምናልባት ቆይተንባቸው ሊፈልጉን ወጥተው ይሆናል ስለዚህ ወደ ጫካ እንሂድ" አሉ፡፡

ዘምዘምም በሃሳቡ ተስማምታ እየሔዱ እያለ አባባ መርጊያን አገኟቸው፡፡ ዘምዘምም ለአባባ ሰላምታ ካቀረበች በኋላ የት ሄደው እነደሆነ ጠየቀቻቸው፡፡ አባባም የሆነውን ሁሉ ነገሯት፡፡ዘምዘምም ድንግጥ ብላ"የዝንጀሮዋ ልጅ ተሰብራ አግኝተናት እርስዎ ባስተማሩን መንገድ ጠግነን ወተት ሰጥተናት ነው የመጣነው" አለቻቸው፡፡ አባባም "ትንሿን ዝንጀሮ ለእናቷ መልሱ አለበለዚ ደቦጭ መሞቱ ነው" አሏቸው፡፡እነሱም ዝንጀሮዋን ይዘው በመሄድ ዛፉ ስር አስቀመጧት፡፡ከዚያም ራቅ አሉ፡፡ዝንጀሮዋም ሰዎቹ በአካባቢው አለነመኖራቸውን አይታ ደቦጭን አስቀምጣ ልጇን ይዛ ወደ ጫካው ገባች፡፡

## አዳምጦ መናገር

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

❖ ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች መሰረት ያሰፈሯቸውን ግምቶች ካዳመጡት ምንባብ ጋር መዛመዱን እንዲገመግሙ እድል ይስጧቸው፡፡

- ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንዳቸውን ግምት ሌሎቹ እንዲገመግሙ ያድርጉ፡፡
- የሰጡት ግምት ከተደመጠው ሀሳብ ጋር ለተዛመደላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ምስሉ ከተደመጠው ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡
- የተማሪዎችን ምላሽ በመመልከት በምስሉ ላይ ካሉ ሰዎች አቀማመጥና ከሚዛኖቹ ጋር አዛምደው ምስሉ ከተደመጠው ጽሑፍ ጋር ያለውን ትስስር ያብራሩላቸው፡፡

- በተማሪ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡
- ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡
- የማዳመጥ ችሎታችን የተሻለ ለማሳደግ የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን ወይም ታሪኮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን ይደግፉ፡፡

**ተግባር ፪**

**መምህር፡-**

- "**ብልኋ ዝንጀሮ**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡
- ሲያነቡላቸው ተማሪዎቹ ዋና ዋና ነጥቦችን እንዲፅፉ ትዕዛዝ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም ያዳመጡትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ ተራ በተራ እየተነሱ እንዲናገሩ ያድረጉ፡፡
- እርማትና ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡

## 🗝 ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ በተመለከተ አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ምሳሌም ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ላሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ አውዳዊ(አገባባዊ) ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተያዩና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ✓ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ ቃላቱ በቃል እየተነበቡላቸው አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡አካቶ ትምህርትን እንደ ሁኔታው ይተግብሩ፡
- ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

### የተግባር ፩ መልስ

| ቃላት | አውዳዊ ፍቺ |
|---|---|
| 1. ቅጠል | የረገፈ የዛፍ አካል |
| 2. የሰፈሩ | የአካባቢው |
| 3. ወላጆች | ቤተሰቦች |
| 4. መደናገጥ | መርበትበት |
| 5. ወጥታ | ዛፍ ላይ ወጥታ |
| 6. ወተት | የላም ተዋፅኦ |

(ሌሎች ተዛማጅ ፍቺዎችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡)

## ተግባር ፪

### መምህር፡-

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ የተዘረዘሩ ቃላት የመነሻ ሆሄያትን በሌላ በመተካት ሌላ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተግባሩን ለማቅለል ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በታዘዙት መልኩ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተግባሩን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው እንደጨረሱም የሰሩትን ሥራ ይዩላቸው፡፡ በሚከተለው መልኩ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

**መልስ፡-**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ጅብ | ልብ | 2. በሬ | ክሬ | 5. ግመል |
| 3. ቀበሮ | ከበሮ | 4. ጉሬዛ | ቃሬዛ | አመል |

## ተግባር ፫

### መምህር፡-

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፫ የተቀመጡትን ምስሎች ከትክክለኛ መጠሪያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የምስሎቹን ሁኔታ በድምፅ ይንገሯቸውና ስማቸውን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተጨማሪ ምስሎችን በማሳዬት የምስሎችን ስም በረብተራቸው እየፃፉ የፅህፈት ክህሎታቸው እንዲጎለብት ይገዟቸው፡፡

# ንባብ

## ጠጣ

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን ጠጣ የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በመጀመሪያ ምንባቡን በግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ አንቀፁን ለተማሪዎች በማከፋፈል በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች ሲያነቡ የሚከተሉትን ነትቦች ከግምት እንዲያስገቡ ሰሌዳ ላ ይፃፉላቸው፡-
  - ሲያነቡ የክፍል ጓደኞቻቸውን በዓይናቸው እንዲቃኙ…
  - የምንባቡን የሐሳብ ፍሰት እንዲጠብቁ..
  - የሚያነቡትን መፅሐፍ በተመጠነ ርቀት እንዲይዙ…
  - ምንባቡን በጣታቸው እንዳይጠቁሙ…
- በንባብ  ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ጠጣ የሚለውን ምንባብ በግል አንብበው ሲጨርሱ ከምንባቡ የተረዱትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## አንብቦ መረዳት

❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባር ፩ መልስ**

7. ሐሰት
8. ሐሰት
9. ሐሰት

## ቃላት

**ተግባር ፩**

- ተማሪዎች በመማሪያ መፅሃፋቸው ላይ ያሉትን በሰንጠረዡ ውስጥ ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ፊደላት በመተቀም ቃላትን እንዲመሰርቱ ይደግፏቸው፡፡
- ምሳሌ በመስጠት ተግባሩን ተረድተው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- በሚከተለው መልኩ እርማት ይስጧቸው፡፡

| የተዘበራረቁ ፊደላት | የተመሰረቱ ቃላት | |
|---|---|---|
| ድ ዝ ል ጣ ሮ | ጦጣ | አንበሳ |
| ብ ን በ ሆ ጠ | ድኩላ | ዋልያ |
| ዋ ር ላ ቀ ጅ | ዝንጀሮ | ቀበሮ |
| ኩ ጆ ኔ ነ ዝ | ቀጭኔ | ነብር |
| ያ ጭ አ ሳ | ጦጣ | ጅብ… |

**ተግባር ፪**

**መምህር፡-**

- በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር ፪ ላይ የቀረቡትን ፊደላት በመጠቀም ሌሎች አዳዲስ ቃላትን እንዲመሰርቱ ይደግፏቸው፡፡
- ሌሎች ተጨማሪ ተግባርም ይስጧቸው፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡
- ተጨማሪ የክፍልና የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፪ መልስ

| | |
|---|---|
| ከ | **ከበሮ፣ ከረሜላ፣ ከረሻት…** |
| ቀ | ቀበሮ፣ ቀበሌ፣ ቀን |
| መ | መስኮት፣ መኪና፣ መፅሐፍ |
| አ | አባት፣ አሳ፣ አስኳል |
| ደ | ደሴት፣ ደብተር፣ ደርዘን |

(ሌሎች ቃላትን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡)

# አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- "ጦጣ" የሚለውን ምንባብ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ይደግፏቸው፡፡
- ተማሪዎች ሲያነቡ፡-
    - ደቂቃ በመመዝገብ ለውጣቸውን ይከታተሉ..
    - በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት አቀላጥፎ ማንበቡን

| የመገምገሚያ መስፈርት | | በመጀመሪያ ንባብ | በሁለተኛ ንባብ |
|---|---|---|---|
| ሀ. | በስህተት የተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ለ. | ተነጥለው የተነበቡ ቃላት ብዛት | | |
| ሐ. | በንባብ ጊዜ የተደገሙ ቃላት ብዛት | | |
| መ. | ተገቢ እረፍት ያልተደረገባቸው ስርዓተ ነጥቦች ብዛት | | |
| ድምር | | | |

## መፃፍ

### ተግባር ፱

**መምህር፡-**

- በተማሪዎች መማሪያ መፅሃፍ ላይ በተቀመጠው ትዕዛዝ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸውና ተማሪዎቹም ወደ ደብተራቸው በማስፈር ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን እንዲያሟሉ ያድርጉ፡፡

1. በግ ፀጉራማ የቤት እንስሳ ነው(፡፡)
2. ንብ ማር ትሰራለች(፡፡)
3. አህያ ለማዳ እንስሳ ነች(፡፡)
4. ነብር የት አገር ይገኛል(?)
5. ምስጋናው ውሻ ሲጮህበት እናቴ ድረሽ ብሎ ጮኸ(!)

# የማጠቃለያ ተግባር

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- በመማሪያ መጽሃፋቸው ላይ ከቀረቡ ልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ ፅሁፍን አንብበው የተጤቁትን መመለስ ነው፤ይህንን ለማሰራት ፅሑፉን አንብበው መልሱን ከምክንያት ጋር እንዲሰጡ ማድረግ፡፡
- ሌሎች ልብ አንጠልጣና አመራማሪ ታሪኮችን በመስጠት እንዲሰሩ ድርጓቸው፡፡
- የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችንም ባማከለ(ባካተተ) መንገድ ተግባራቱን ያሰሯቸው፡፡ሠ
- እርማት ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፪

- በመማሪያ መፅሐፍ ላይ እንደተቀመጠው ተማሪዎች የተሌዩ ምንጮችን በማገናዘብ ስለ አንድ ቤት እንስሳ ባህርይ እና ሁኔታ ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- እርስዎ ስለ በግ የሚከተለውን ሐሳብ ያንብቡላቸው፡-

## ተግባር ፫

**መምህር፡-**

- በመማሪያ መፅሃፍ በተግባር ፫ ላይ የቀረበውን ሰንጠረዥ በትእዛዙ መሰረት እንዲያሟሉ ያድርጉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዶሮ | ድኩላ | ድመት | ላም | የሜዳ አህያ |
| ሰጎን | በሬ | ቀበሮ | ዝሆን | በግ |

| የቤት እንስሳት | የዱር እንስሳት |
|---|---|
| ዶሮ | ቀበሮ |
| በሬ | ሰጎን |
| ድመት | ድኩላ |
| ላም | ዝሆን |
| በግ | የሜዳ አህያ |

እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡